በገንዘብ ሚኒስቴር በወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ አፈጻጸም ላይ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

መጋቢት 2011 ዓ/ም
አዲስ አበባ

መውጫ

ድርሞ /Excutive Summery/ 1
ክፍል አንድ 4
መግቢያ 4
የገንዘብ ሚኒስቴር አመሰራረት 4
የገንዘብ ሚኒስቴር 5
ራዕይ 5
ተልዕኮ 5
የገንዘብ ሚኒስቴር ተግባርና ኃላፊነት 5
የገንዘብ ሚኒስቴር ድርጅታዊ መዋቅር እና የሰው ኃይል 6
ድርጅታዊ መዋቅር 6
የሰው ኃይል 6
የኢትዮጵያ ወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ የፋይናንስ ምንጭ 7
የኦዲቱ አላማ 7
ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ 7
ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች 7
እና የኦዲት መመዘኛ መስፈርት 7
የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች 7
የኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ 8
የኦዲቱ ወሰን 8
የኦዲቱ ዘዴ 8
የአሰራር ስርአት መግለጫ 10
ክፍል ሁለት 11
ግኝቶች 11
ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ አዋጅ የአፈጻጸም መመሪያ ስለማውጣቱ በተመለከተ 11
ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመመካከር 18
ደንቦችና ሁኔታዎችን መወሰኑን በተመለከተ 18
የሚኒስቴር መ/ቤቱ አደረጃጀት እና የመረጃ ልውውጥ ስርአትን 22
በተመለከተ 22
ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፈንዱን አጠቃቀም ሪፖርት ማቅረቡን 23

በተመለከተ 23

ሚንስቴር መ/ቤቱ የየክልሎችን የፈንድ ድርሻ በማስላት 25

ማሳወቁን በተመለከተ 25

ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከባንኩ በሚቀርብለት ጥያቄ መሠረት ከተጠቃለለው ፈንድ ላይ ክፍያ መፈጸሙን በተመለከተ 28

ሚንስቴር መ/ቤቱ በክልሎች እና በከተማ መስተዳድር የፋይናንስ ቢሮዎች በፈንዱ አፈፃፀም ዙሪያ ክትትል እና ቁጥጥር ማድረጉን በተመከለተ 30

ክፍል ሦስት 33

የኦዲቱ መደምደሚያ (Audit Conclusion) 33

ክፍል አራት 35

የኦዲቱ ማሻሻያ ሀሳብ (Recommendation) 35

አባሪዎች i

አባሪ 1- የገንዘብ ሚኒስቴር የመመዘኛ መስፈርት i

ድርሞ /Excutive Summery/

ኦዲቱ የተከናወነው የመንግሥት መ/ቤቶችን የክዋኔ ኦዲት ለማድረግ ለፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በአዋጅ ቁጥር 982/2008 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ሲሆን የክዋኔ ኦዲቱ አላማ የገንዘብ ሚኒስቴር የወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ አፈጻጸም በብቃትና ውጤታማ በሆነ መልኩ እየተከናወነ ስለመሆኑ ለመገምገም ሲሆን በዚሁ መሰረት በኦዲቱ የተገኙ ዋና ዋና ግኝቶች የሚከተሉት ናቸው፣

1. የገንዘብ ሚኒስቴር ህጋዊ የሆነ የአፈጻጸም መመሪያ በወቅቱ በማዘጋጀት ስራ ላይ እንዲውል ባለማድረጉ ለወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ ከተመደበው 10 ቢሊዮን ብር ውስጥ ከ9.1 ቢሊዮን ብር በላይ በአዋጁ ስልጣን ባልተሰጣቸው አካላት በተዘጋጁ ፣ባልጸደቁና ህጋዊነታቸውን ጠብቀው ስራ ላይ እንዲውሉ ባልተደረጉ መመሪያዎች ለተጠቃሚዎች እንዲሰራጭ ማድረጉ፡፡
2. የገንዘብ ሚኒስቴር ለወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ ከተመደበው 10 ቢሊዮን ብር ውስጥ ከ9.1 ቢሊዮን ብር በላይ ገንዘቡ ለተጠቃሚዎች እስከ ተሰተጠበት ጊዜ ድረስ በአዋጁ መሰረት የፈንዱን ገንዘብ በአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት በኩል ለተጠቃሚዎች የሚተላለፍበት ደንቦችና ሁኔታዎች ያላዘጋጀ መሆኑ፡፡
3. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድን በተመለከተ በአዋጅ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት ለመወጣት የሚያስችል አደረጃጀት እና የመረጃ ልውውጥ ስርአት ያለው ቢሆንም የፈንዱን አፈጻጸም ህጋዊና ውጤታማ ለማድረግ በአዋጅ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት ተግባራዊ ለማድረግ በተሟላ ሁኔታ /ማለትም መመሪያና ደንብ ማዘጋጀት ያለባቸው የስራ ክፍሎች ሳያዘጋጁ፣ ለሚኒስትሮችና ለተወካዮች ምክር ቤቶች የፈንዱን ገንዘብ አፈጻጸም ሪፖርት ማቅረብ የሚገባቸው የስራ ክፍሎች ያላቀረቡ መሆናቸው.../ ስራ ላይ እንዲውል አለማድረጉ፤ እንዲሁም ለተጠቃሚዎች የተላለፈው ከ9.1 ቢሎዮን ብር በላይ አፈጻጸም እና ውጤታማነት በተመለከተ ከባንኩ ወይም ከአዋጁ ውጪ ባንኩ ከወከላቸው የክልሎችና የከተማ መስተዳድር ፋይናንስ ቢሮዎች በአዋጁ በተቀመጠ የጊዜ ሰሌዳ መሰረት በ2009 እና በ2010 በጀት አመት የመረጃ ልውውጥ ያላደረገ መሆኑ፡፡

4. በወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ አዋጅ መሰረት የገንዘብ ሚኒስቴር ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በሚደርሰው **የፈንዱን አጠቃቀም መግለጫና ሪፖርት** በተጠቃለለው ዓመታዊ የመንግስት ሂሣብ ሪፖርት ውስጥ በማካተት በ2009 እና በ2010 በጀት ዓመት በየደረጃው ለሚኒስትሮች ምክር ቤት እና ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያላቀረበ መሆኑ፡፡

5. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የየክልሉን ወጣቶች ቁጥር መሠረት በማድረግ ከፈንዱ ገንዘብ ላይ ለየክልሉ ሊከፋፈል የሚገባውን ድርሻ በማስላት በአዋጅ ስልጣን ለተሰጠው ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በተሟላ መልኩ ማሳወቅ ሲገባው፣ ከ10 ቢሊዮን ብር ውስጥ 5 ቢሊዮን ብር ብቻ ነው ባንኩ እንዲያውቀው መደረጉ፣ በመሆኑም ሙሉ በሙሉ የክልሎችን ድርሻ የማሳወቅ ስራ ሳይሰራ ከ9.1 ቢሊዮን ብር በላይ የፈንዱ ገንዘብ ከመንግስት ካዝና ወጪ ሆኖ ለተጠቃሚዎች እንዲተላለፍ ተደርጓል፡፡

6. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በተዘዋዋሪ ፈንድ አዋጅ ቁጥር 995/2009 አንቀጽ 6/2 መሠረት ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በሚቀርብለት ጥያቄ መሠረት ከተጠቃለለው ፈንድ ላይ ክፍያ መፈጸም ሲገባው፣ በአዋጁ ስልጣን ላልተሰጣቸው ለዘጠኙ ክልሎችና ለሁለቱ ከተማ መስተዳድር የፋይናንስ ቢሮዎች ከ9.1 ቢሊዮን ብር በላይ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፡፡

7. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የዘጠኙ ክልሎች፣ የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተማ መስተዳድር የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮዎች ተፈጻሚ እንዲያደርጉት በሰጠው አቅጣጫ መሰረት፣ ከአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት ጋር በገቡት የገንዘብ አስተዳደር ውል መሰረት የፈንዱን ገንዘብ ለአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት ማስተላለፋቸውን ክትትል እና ቁጥጥር ያላደረገ መሆኑ፡፡

8. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለዘጠኙ ክልሎች፣ ለአዲስ አበባ እና ለድሬዳዋ ከተማ መስተዳድር የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮዎች አዋጁ ከሚፈቅደው ውጪ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ውክልና ተፈጻሚ እንዲያደርጉ በቀን 01/10/2009 ዓ/ም በደብዳቤ ቁጥር ማኢ-30/19/12 ማዘዙ፣እንዲሁም የሚኒስቴር መ/ቤቱ በሰጠው አቅጣጫ መሰረት፣ ስለ ፈንዱ ገንዘብ አጠቃቀም ከአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት የሚቀርብላቸውን ሪፖርት በማጠቃለል በየስድስት ወሩ እንዲሁም **የተመረመረ የፈንዱን ሂሳብ ከተሰጠው የኦዲት አስተያየት** ጋር በየአመቱ ሂሳቡ በተመረመረ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ በፌደራል

መንግስት የበጀት አመት መሰረት ለገንዘብ ሚኒስቴር እንዲያቀርቡ ክትትል እና ቁጥጥር አለማድረጉ እና ክልሎችም የሚጠበቅባቸውን ያልፈጸሙ መሆኑ፡፡

ክፍል አንድ

መግቢያ

የገንዘብ ሚኒስቴር አመሰራረት

9. የዛሬው የገንዘብ ሚኒሰቴር ከአንድ መቶ አመት በፊት ጥቅምት14/1900 ዓ.ም. በዳግማዊ አፄ ምኒልክ ዘመነ መንግስት “የገንዘብና የጓዳ ሚኒሰቴር” በሚል መሰረቱን ጥሎ የተለያዩ ታሪካዊ ሂደቶችን በማለፍ ለረጅም ዓመታት ተግባሩን እያከናወነ ይገኛል፡፡
10. መ/ቤቱ የሀገሪቱን የልማት እቅድ መቀመር፣ በጀት ማዘጋጀት ማስፀደቅና ማስተዳደር፣ የእቅድና በጀት አፈፃፀምን መከታተልና መገምገም እንዲሁም ፈጣንና ዘላቂ ልማትን ለማረጋገጥ የተዘጋጁትን ዕቅዶች እውን ለማድረግ የአገር ውስጥ ፋይናንስ ግኝትን ማጎልበት እንዲሁም የውጭ ሀብት የማሰባሰብና በስራ ላይ በአግባቡ እንዲውል የማድረግ ተግባራትን እያከናወነ ይገኛል፡፡ ለፈጣን ኢኮኖሚ ዕድገት የተረጋጋ ማክሮ ኢኮኖሚ መኖር አስፈላጊ እንደመሆኑ በማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲና ማኔጅመንት በኩልም የራሱን ድርሻ በመወጣት ላይ ይገኛል፡፡
11. የኢትዮጵያ ፌዴራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ስራ ላይ በቆየባቸው ዓመታት ያጋጠሙ የአፈፃፀም ችግሮችን ለማስወገድ እንዲሁም ቀልጣፋ እና ውጤታማ ለማድረግ በተለያዩ ጊዜ አዋጆች እና ማሻሻያዎች ተደርገዋል፡፡
12. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ቀድሞ የነበረው አዋጅ ቁጥር 648/2001 የኢትዮጵያ ፌዴራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን ማሻሻል በማስፈለጉ አዋጅ ቁጥር 970/2008 የፋይናንስ አስተዳደር ማሻሻያ አዋጅ ታውጇል፡፡
13. የልማት ግቦቻችን ስኬት በሀገራችን የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ውስጥ የወጣቶችን ቀጥተኛ ተሳትፎ የሚጠይቅ በመሆኑ፤ የወጣቶችን ሁለንተናዊ ተሳትፎ እና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ በገቢ ማስገኛ እንቅስቃሴዎች ተደራጅተው ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮቻቸውን እንዲያቃልሉ የገንዘብና የቴክኒክ ድጋፍ ማድረግ በማስፈለጉ፤ ወጣቶች ያላቸውን ዕምቅ የማምረት አቅም ተጠቅመው በሀገሪቱ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ውስጥ ቀጥተኛ ተሳታፊ መሆን እንዲችሉ የሚያስፈልገውን የገንዘብ ድጋፍ ለማቅረብ

የወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድን ማቋቋም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀጽ 55 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ታወጇል፡፡

14. በአዋጅ ቁጥር 995/2009 ዓ/ም የኢትዮጵያ ወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ ለማቋቋም በወጣው አዋጅ መሰረት የገንዘብ ሚኒስቴር፣ የሴቶች፣ ህጻናትና ወጣቶች ሚኒስቴር እና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በቅደም ተከተል ፈንዱን ለማስተግበር መመሪያና ደንቦች የማውጣት፣ በፈንዱ ዙሪያ ተግባር እና ኃላፊነት ያላቸውን አካላት የማስተባበርና የመደገፍ እንዲሁም ፈንዱን የማስተዳደር ስልጣን የተሰጣቸው ቢሆንም በአዋጁ የተሰጣቸውን ተግባርና ኃላፊነቶች ተግባራዊ ከማድረግ አንጻር ክፍተቶች ስላሉ እና የክዋኔ ኦዲቱ ማከናወን አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ በሦስቱ የመንግስት መ/ቤቶች የኦዲት ስራው ተከናወኗል፡፡

15. የኦዲት ሪፖርቱ በገንዘብ ሚኒስቴር፣ በሴቶች፣ ህጻናትና ወጣቶች ሚኒስቴር እና በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በተናጠል የሚሰራ ሲሆን፤ ቀጥሎ የቀረበው የኦዲት ሪፖርት የገንዘብ ሚኒስቴር ላይ የተሰራ ነው፡፡

የገንዘብ ሚኒስቴር

ራዕይ

16. ኢትዮጵያ በ2017 መካከለኛ ገቢ ያላት ሀገር እንድትሆን ሀብትን ውጤታማና ፍትሃዊ በማድረግ መሪ ተቋም ሆኖ ማየት፣

ተልዕኮ

17. ፈጣን፣ ዘላቂና ፍትሃዊ ልማትን ተደራሽ ለማድረግ የሚያስችሉ የፊስካል ፖሊሲዎችን መቅረፅ፣ የኢኮኖሚ ትብብር በማጠናከር የውጭ ሀብት ማሰባሰብና ማስተዳደር፣ዘመናዊ፣ ቀልጣፋ፣ ውጤታማና ተጠያቂነት ያለው የመንግሥት ፋይናንስ አስተዳደርና ቁጥጥር ሥርዓት መዘርጋት ነው፡፡

የገንዘብ ሚኒስቴር ተግባርና ኃላፊነት

18. ቀጥለው የተዘረዘሩት ለገንዘብ ሚኒስቴር በተዘዋዋሪ ፈንድ አዋጅ ቁጥር 995/2009 የተሰጡ ተግባርና ኃላፊነቶች ናቸው፡-

- የየክልሉን ወጣቶች ቁጥር መሠረት በማድረግ ከፈንዱ ገንዘብ ላይ ለየክልሉ ሊከፋፈል የሚገባውን ድርሻ በማስላት ለባንኩ ያሳውቃል፤

- ባንኩ የፈንዱን ገንዘብ በአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት በኩል ለተጠቃሚዎች የሚያስተላልፍበትን ደንቦችና ሁኔታዎች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመመካከር ይወስናል፤
- በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6/2 መሠረት ከባንኩ በሚቀርብለት ጥያቄ መሠረት ከተጠቃለለው ፈንድ ላይ ክፍያ ይፈጽማል፤
- ከባንኩ የሚደርሰውን የፈንዱ አጠቃቀም መግለጫና ሪፖርት በተጠቃለለው ዓመታዊ የመንግስት ሂሣብ ሪፖርት ውስጥ በማካተት በየደረጃው ለሚኒስትሮች ምክር ቤት እና ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያቀርባል፡፡

የገንዘብ ሚኒስቴር ድርጅታዊ መዋቅር እና የሰው ኃይል

ድርጅታዊ መዋቅር

19. የገንዘብ ሚኒስቴር ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስትሩና ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ሆኖ በሚኒስቴር እና በሁለት ሚኒስቴር ዴኤታ እና በሶስት የሚኒስትር አማካሪዎች እንዲሁም ሀያ አራት ዳይሬክቶሬቶች ተዋቅሯል:: በተጨማሪ የመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ፣ የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት፤ የመንግስት የልማት ድርጅት ባለአደራ ቦርድ እና የኢትዮጵያ ሒሳብ አያያዝ ቦርድ ጽ/ ቤት ተጠሪነታቸው ለገንዘብ ሚኒስቴር ነው፡፡ የወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የመንግስት ሂሳብ ዳይሪክቶሬት፣ በህግ አገልግሎት ዳይሪክቶሬት፣ በፊሲካል ፖሊሲ ዳይሪክቶሬት፣ በትሬዠሪ ዳይሪክቶሬት፣ በእንስፔክሽን ዳይሪክቶሬት፣ እንዲሁም በበጀት ዳይሪክቶሬት ይከናወናል፡፡

የሰው ኃይል

20. ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የተፈቀደለት አጠቃላይ የሥራ መደብ 1074 ሲሆን አሁን ያለው የሰው ሀይል ሴት 250 እና ወንድ 363 ሰራተኞች በጠቅላላው 613 ነው፡፡ በትምህርት ደረጃ ሲተነተን ፒ.ኤች.ዲ 2፣ ሁለተኛ ዲግሪ 78፣ የመጀመሪያ ዲግሪ 248፣ ዲፕሎማ ቴክኒክና ሙያ 60፣ እንዲሁም 12 ክፍል እና ከዚያ በታች 225 መሆናቸው ከሰው ሀብት ልማት ሪከርድና ጠቅላላ አገልግልት የስራ ሂደት ከተሰበሰበ መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡

የኢትዮጵያ ወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ የፋይናንስ ምንጭ

21. የኢትዮጵያ ወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ ብር 10 ቢለዮን ሲሆን የፋይናንስ ምንጭ ከመንግስት በጀት ነው፡፡

የኦዲቱ አላማ

22. በገንዘብ ሚኒስቴር የወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ አፈጻጸም በብቃትና ውጤታማ በሆነ መልኩ እየተከናወነ ስለመሆኑ ለመገምገም ሲሆን በስራው ወቅት የተከሰቱ የአሰራር ችግሮች ካሉ መንስኤያቸውን በመለየት ችግሮችን ለማስወገድ ወይም ለመቀነስ የሚያስችል የማሻሻያ ሃሳቦችን በማቅረብ ተጠያቂነትን ለማስፈን ነው፡፡

ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ

23. ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ "የወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ አፈጻጸም ብቃት ባለውና ውጤታማ በሆነ መልኩ እየተከናወነ መሆኑን መገምገም" የሚል ነው፡፡

ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች እና የኦዲት መመዘኛ መስፈርት

የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች

24. ከላይ በተለየው የኦዲት አካባቢ ሥር አንድ ዋና እና ሦስት ንዑስ የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች /Audit Issues/ ተለይተዋል፡፡ እነሱም ፡-

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአዋጅ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት ለመወጣት የሚያስችል መመሪያና ስታንዳርድ ስለመኖሩና ተግባራዊ ስለማድረጉ መገምገም፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአዋጅ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት ለመወጣት የሚያስችል መዋቅር፣ የሰው ኃይልና የመረጃ ልውውጥ ስርአት ያለው ስለመሆኑ መገምገም፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአዋጅ የተሰጡትን ዝርዝር ተግባራት ብቃት ባለው፣ በተቀላጠፈና ውጤታማ በሆነ መልኩ ስለመተግበሩ መገምገም፡፡

የኦዲቱ መመዘኛ መስፈርቶች

25.የኦዲት ቡድኑ እነዚህን የትኩረት አቅጣጫዎች ለመገምገም የሚረዱ 9 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶችን (Evaluative criteria) አዘጋጅቷል፡፡ በተዘጋጁት የትኩረት አቅጣጫዎችን እና የመመዘኛ መስፈርቶች ላይም የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች አስተያየታቸውን እንዲሰጡበት ቀርቦላቸው ስምምነት ላይ ተደርሷል፡፡ የገንዘብ ሚኒስቴር ኦዲት መመዘኛ መስፈርት **በአባሪ 1** ተያይዟል፡፡

የኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ

የኦዲቱ ወሰን

26.በአጠቃላይ ኦዲቱ የተከናወነው በገንዘብ ሚኒስቴር፣ በሴቶች፣ ህጻናት እና ወጣቶች ሚኒስቴር እንዲሁም በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሲሆን የሸፈነው ጊዜ የወጣቶች ተዘዋዋሪ ብድር ፈንድ በአዋጅ ከተቋቋመበት ከመጋቢት 2009 ዓ/ም እስከ 2010 በጀት አመት ያለው የሥራ አፈጻጸም ነው፡፡ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት በያንዳንዳቸው መ/ቤቶች በተናጠል ተዘጋጅቶ የቀረበ ሲሆን፤ ይህ ሪፖርት የገንዘብ ሚኒስቴር በአዋጁ በተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት መሰረት ተዘጋጅቶ የቀረበ ነው፡፡

የኦዲቱ ዘዴ

27.ኦዲቱ የተከናወነበት ዘዴ እንደሚከተለው ነው፡-

- ኦዲቱ በዋናነት መሰረት ያደረገው የወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ አዋጅ ቁጥር 995/2009 እንዲሁም የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ለዘጠኙ ክልሎችና ለሁለቱ ከተማ መስተዳድሮች የፋይናንስ ቢሮዎች በአዋጅ የተሰጠውን ፈንዱን የማስተዳደር ስልጣን በውክልና ያስተላለፈባቸው ሰነዶች እና ገንዘብ ሚኒስቴር ይህንን የውክልና ሰነድ ክልሎችና ከተማ መስተዳድሮች እንዲተገብሩት መመሪያ ያስተላለፈበት ሰነዶች በመከለስ፤
- በትግራይ፣ አማራ፣ ኦሮሚያ፣ ሀረሪ ክልሎች እንዲሁም በአዲስ አበባና ድሬደዋ ከተማ መስተዳድሮች የሚገኙ የፋይናንስ ቢሮዎች፣ የማይክሮ ፋይናንስ

ተቋማት፣ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንትርፕራይዝ ቢሮዎች፣ የወጣቶችና ስፖርት ቢሮዎች እንዲሁም የተወሰኑ ብድር ወስደው ወደ ስራ የገቡ በትግራይ፣ ድሬደዋ፣ ሀረሪ ክልሎች እና በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር የሚገኙ የተወሰኑ ኢንተርፕራይዞችን በአካል ተገኝቶ በመመልከት እና ቃለ መጠይቅ በማቅረብ፣ የሰነድ ማስረጃዎች በመሰብሰብ እና በመተንተን፣

- የወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር ዕቅድና ዕቅድ ክንውን፣ የማኔጅመንት ቃለ ጉባኤዎች እና ክልሎች፣ ከከተማ መስተደዳድሮች እና ከገንዘብ ሚኒስቴር እና የወጣቶች የልማትና የውጤት ፓኬጅ ተግባራዊ ለማድረግ የፌዴራል የክልል መንግስትና እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ያካተተ ሀገራዊ ስትሪንግ ኮሚቴ ሪፖርት በፌዴራል ተቋማት በክልልና በከተማ አስተዳደር ውይይት መድረክ ላይ የተነሱ ዋና ዋና ነጥቦች፤
- በገንዘብ ሚኒስቴር የፈንዱን መመሪያዎች፣ ደንቦች እና ሁኔታዎች በተመለከተ ከህግ አገልግሎት ዳይሪክቶሬት በ11/11/2010 ለኦዲቱ የቀረበ ሰነድ፣ ከብሄራዊ ፕላን ኮሚሽን የሥነ ሕዝብና ስታትስቲክስ ዳይሪክቶሬት ዳይሪክተር የዘጠኙ ክልሎችና የሁለቱ ከተማ መስተዳድሮች ከ18-34 ዓመት ዕድሜ ክልል ያሉ የወጣቶች ብዛት የሚያሳይ ሰነድ፣
- በገንዘብ ሚኒስቴር ለዘጠኙ ክልሎችና ለሁለቱ ከተማ መስተዳድሮች የተደረገው የፈንዱ የገንዘብ መጠን ክፍፍል የሚያሳይ ሰነድ፣ እንዲሁም ለሦስቱም ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች የሚመለከታቸው ኃላፊዎችና ባለሙያዎች የቀረበላቸውን ቃለ መጠይቅ፤
- እና ሌሎች አግባብነት ባለው መልኩ የተሰበሰቡትን ማስረጃዎች እና መረጃዎች በመከለስ /በመተንተን/   አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡

የአሰራር ስርአት መግለጫ

28.የኢትዮጵያ ወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ የአሰራር ስርአት መግለጫ የተዘጋጀው በኦዲቱ ሲሆን በስዕላዊ መግለጫ ይህን ይመስላል፡፡



ክፍል ሁለት

ግኝቶች

ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ አዋጅ የአፈጻጸም መመሪያ ስለማውጣቱ በተመለከተ

29. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ አዋጅ ቁጥር 995/2009 የአፈጻጸም መመሪያ ሊያወጣ እና የሚመለከታቸው አካላት በስራ ላይ እንዲያውሉት ሊያደርግ እንደሚገባ በአዋጅቁጥር995/2009 አንቀፅ 16 ተደንግጓል፡፡

30. ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ይህን በአዋጅ የተሰጠውን ሃላፊነቱን ስለመወጣቱ ኦዲት ሲደረግ የኦዲት ቡድኑ ጉዳዩን አስመልክቶ ባካሄዳቸው የዶክመንት ክለሳዎች እና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የስራ ሃላፊዎች፣ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የስራ ሃላፊዎች፣ የክልል የፋይናንስ ቢሮ የስራ ሃላፊዎች፣ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የፋይናንስ ተቃማት የስራሃላፊዎች እና ከባለድርሻ አካላት ጋር ባካሄዳቸው ቃለ መጠይቆች መሰረት ሚኒስቴር መስሪያቤቱ የወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ አዋጁ ቁጥር995/2009 ስራ ላይ ለማዋል የሚያስችል መመሪያ እንዳላወጣ እና በአዋጁ የተሰጠውን ሃላፊነት እንዳልተወጣ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

31. በሌላ መልኩ በአዋጁ መሰረት መመሪያው በገንዘብ ሚኒስቴር መዘጋጀት ሲገባው ኃላፊነት ባልተሰጠው አካል በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የካቲት 2009 ዓ/ም የተዘጋጀ ማህተምና ፊርማ የሌለው የኢትዮጵያ ወጣቶች የዕድገትና የልማት ፓኬጅ የወጣቶች የተዘዋዋሪ ብድር ፈንድ አስተዳደር መመሪያ ስራ ላይ እንዲውል በማድረግ እየተጠቀሙበት መሆናቸውን ማህተምና ፊርማ የሌለው ሰነድ በማስረጃነት በማቅረብ የገንዘብ ሚኒስቴር የሚመለከታቸው ኃላፊዎች በ15/09/2010 ዓ/ም በተደረገላቸው ቃለ መጠይቅ ገልጸዋል፤፤ ይሁንእንጂ የኦዲት ቡድኑ ጉዳዮን አስመልክቶ ባካሄደው መጣራት መመሪያው ስራ ላይ እንዲውል በገንዘብ ሚኒስቴር ወይም አዘጋጅቶታል በተባለው አካል በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አቅጣጫ ስለመሰጠቱ የሚያሳየው ደብዳቤ. ማህተም ወይም ፊርማ የሌለው እና ያልጸደቀ ረቂቅ መሆኑን፣ ለማረጋገጥ ችላል ፡፡

32..ከዚህ በተጨማሪ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የካቲት 2009 ዓ/ም የተዘጋጀው የኢትዮጵያ ወጣቶች የዕድገትና የልማት ፓኬጅ የወጣቶች የተዘዋዋሪ ብድር ፈንድ አስተዳደር መመሪያ በረቂቅ ደረጃ ተዘጋጅቶ የነበረ ቢሆንም ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በወቅቱ መግባባት ላይ ስላልተደረሰ መመሪያው ያልጸደቀና ስራ ላይ እንዲውል ያልተደረገ መሆኑን በቀን 25/11/2010 ዓ/ም የሚመለከታቸው የባንኩ ኃላፊዎች ገልጸዋል፡፡

33.በሌላ መልኩ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ መመሪያው የተዘጋጀው የካቲት 2009 ዓ/ም ሲሆን የኢትዮጵያ ወጣቶች ተዘዋዋሪ ብድር ፈንድ 995/2009 አዋጅ የታወጀውና ስራ ላይ የዋለው መጋቢት 1 ቀን 2009 ዓ/ም በመሆኑ መመሪያው አዋጁ ከመጽደቁ በአንድ ወር ቀድሞ ስራ ላይ እንዲውል የተደረገ ስለሆነ የትኛውን አዋጅ መሰረት አድርጎ እንደተዘጋጀ እንደማይታወቅ፣ የኦዲት ቡድኑ አረጋግጧል፡፡

34.ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች በኦዲቱ ነባራዊ ሁኔታ ላይ ፈንዱ የሚተዳደርበት መመሪያን በተመለከተ ምላሽ አልተሰጠም፡፡ ሆኖም የሚመለከታቸው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በኦዲቱ የመውጫ ስብሰባ በሰጡት ምላሽ አዋጁ የገንዘብ ሚኒስቴር መመሪያ ሊያወጣ ይችላል እንጂ በቀጥታ ያወጣል እንደማይል፣ ነገር ግን መመሪያው ባለመውጣቱ በፈንዱ አፈጻጸም ማየት እንደሚቻል፣ እንዲሁም በወቅቱ የወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ ተፈጻሚ ለማድረግ የነበረው ጫና መመሪያው ቀድሞ እንዳይወጣ ምክንያት እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

35.የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በመውጫ ስብሰባው ይህንን ይበሉ እንጂ ከ9.1 ቢሊዮን ብር በላይ የመንግስት ገንዘብ ያለ መመሪያ ወጪ ሆኖ ለተጠቃሚዎች እንዲሰራጭ መደረጉ እንዲሁም ከዚህም የተነሳ የፈንዱ አፈጻጸም በየክልሉ ወጥ እንዳይሆን ከማድረጉም በላይ አፈጻጸሙ በሚጠበቀው ልክ ውጤታማ እናዳይሆንና ከታች የተዘረዘሩት በርካታ ችግሮች እንዲከሰቱ ትልቅ ድርሻ ያለው በመሆኑ የተሰጠው ምላሽ ለኦዲቱ አጥጋቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

36.የገንዘብ ሚኒስቴር በአዋጅ በተሰጠው ተግባር እና ኃላፊነት መሰረት ፈንዱ የሚተዳደርበት መመሪያ ባላዘጋጀበት ሁኔታ ከ9.1 ቢሊዮን ብር በላይ የፈንዱ ገንዘብ ወጪ ሆኖ ለተጠቃሚዎች የተሰራጨ መሆኑን ቀጥለው በተዘረዘሩ በማስረጃ የተደገፉ የኦዲት ግኝቶች ለመረዳት ተችሏል፡፡

- ምንም እንኳን የአዲስ አበባ አስተዳደር የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ፣ የኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት መስተዳድር የገ/የኢኮ/ትብብር ቢሮ፣ የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የፋይናንስና ፕላን ቢሮ፣ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የገ/ኢ/ትብብር ቢሮ የወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ የተመደበውን በጀት የማስተዳደር ስልጣን በአዋጁ የተሰጣቸው ባይሆንም አዋጁ ከሚያዘው ውጪ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በተቀበሉት ውክልና እስከ ጥር 2011 ዓ/ም በቅደም ተከተል ብር 418,830,998.5፣ ብር 3,096,762,848.98፣ ብር 421,261,079.5፣ ብር 2,677,069,826.33 ከገንዘብ ሚኒስቴር ተቀብለው ብድር ለሚገባቸው ወጣቶች እንዲሰጡ፤ ለአዲስ ብድርና ቁጠባ ተቋም አ/ማህበር፣ ለኦሮሚያ ብድርና ቁጠባ ተቋም አ/ማህበር፣ ለደደቢት ብድርና ቁጠባ ተቋም አ/ማህበር፣ ለአማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም አ/ማህበር ሙሉ በሙሉ ማስተላለፋቸውን ለኦዲቱ ከቀረቡ ማስረጃዎችና ለሚመለከታቸው የቢሮው ኃላፊዎችና ባለሙያዎች በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ከሰጡት መልስ ለመረዳት ተችሏል፡፡
- ሆኖም ገንዘቡ የሚተዳደርበትን መመሪያ በአዋጁ መሰረት ማውጣት የነበረበት የገንዘብ ሚኒስቴር ቢሆንም እስከዚህ ጊዜ ድረስ መመሪያውን እንዳላወጣና የክልል ፋይናንስ ቢሮዎች ገንዘቡን ለማስተዳደር እንደ መመሪያ የሚጠቀሙበት፤ በአዲስ አበባ አስተዳደር የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ እና በአዲስ ብድርና ቁጠባ ተቋም አ/ማ መካከል፣ የኦሮሚያ/ክ/መ/መስተዳድር የገ/የኢኮ/ትብብር ቢሮ ከኦሮሚያ ብድርና ቁጠባ ተቋም አ/ማህበር ጋር፣ የትግራይ ብ/ክ/መ/የፋይናንስና ፕላን ቢሮ ከደደቢት ብድርና ቁጠባ ተቋም አ/ማ ጋር፣ እንዲሁም የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት /የገ//ኢ/ት/ቢሮ ከአማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም አ/ማህበር ጋር የተለያዩና ወጥ ያልሆኑ ውሎች አዘጋጅተው በመዋዋል እና ውሉን እንደ መመሪያ በመጠቀም ስራውን እየሰሩ የሚገኙ መሆኑናቸውን የሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች በኦዲቱ በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ የውሉን ሰነዶች በማስረጃነት በማቅረብ ገልጸዋል፡፡
- የወጣቶች እና ስፖርት ሚኒስቴር፣ የትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የወጣቶች እና ስፖርት ቢሮ የወጣቶች ብቃት ማሳደግ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር፣ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የወጣቶች እና ስፖርት ጉዳይ ቢሮ ጸድቆ ስራ ላይ እንዲውል

የተደረገ በሚመለከተው አካል የተዘጋጀ የወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ መመሪያ ባለመኖሩ ባልጸደቀና በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የካቲት 2009 ዓ/ም የተዘጋጀ የኢትዮጵያ ወጣቶች የዕድገትና የልማት ፓኬጅ የወጣቶች የተዘዋዋሪ ብድር ፈንድ አስተዳደር መመሪያ ስራ ላይ እንዲውል በማድረግ እየተጠቀሙበት መሆናቸው ሰነዱን በማስረጃነት በማቅረብ የሚመለከታቸው ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ገልጸዋል፡፡

37.በተጨማሪም በሁሉም ክልል እና ተቋማት ተግባራዊ የሚሆን ወጥነት ያለው ሀገራዊ መመሪያ ባለመዘጋጀቱ የፈንዱ ተጠቃሚ በሆኑ ወጣቶች ላይ ቀጥለው የተዘረዘሩ ችግሮችን የፈጠረ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ከተደረጉ ቃለ መጠይቆች እና ከተሰበሰቡ ማስረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡-ለማሳያ ያክል፡-

- በአንድ ኢንተርፕራይዝ ተደራጅተው ብድር መውሰድ ያለባቸው ወጣቶች ቁጥር መጠን እና የሚደራጁበት ሁኔታ በመመሪያው ባለመገለጹ አንዳንድ ወረዳዎች በኢንተርፕራይዝ ተደራጅተው ብድር የሚወስዱ ወጣቶች ብዛት 5 ብቻ በማደራጀት፣ አንዳንድ ወረዳዎች ደግሞ በ12 አንዳንድ ወረዳዎች በ30 ወዘተ እንደሆነና የሚደራጁ ወጣቶችም በባህሪ የሚተዋወቁ በጋራ ተስማምተው መስራት የሚችሉ ስለመሆናቸው ስምምነት ላይ ደርሰው በራሳቸው የተደራጁ ሳይሆኑ በቦታው ባሉ አመራሮች የሚደራጁ በመሆናቸው ስራውን ተስማምተውና ተናበው እንዳይሰሩ ከሚያደርጓቸው ምክንያቶች አንዱ ሆኖ መገኘቱ፣
- በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር የተዘዋዋሪ ብድር ፈንድ ተጠቃሚ የሆኑ ኢንተርፕራይዞች ላይ በተደረገ የመስክ ምልከታ በተገኘው መረጃ መሰረት፡-
  - ✓ በአራዳ ክ/ከተማ በወረዳ 01 የሚገኝ ሊዲያ ይኩኖና ጓደኞቻቸው የምግብ ዝግጅት ስራ ኢንተርፕራይዝ ተደራጅተው ብድር የወሰዱ የወጣቶች ብዛት 30 ሲሆን አሁን በስራው ላይ የሚገኙ አባላት ብዛት 22 ብቻ መሆናቸው እና በማህላቸው ከፍተኛ የሆነ አለመግባባት በመፈጠሩ ስራውን በአግባቡ መስራት ባለመቻላቸው ለኦዲት ምልከታ በተሄደበት በታሕሳስ 08/2011 ዓ/ም ከሦስት ቀን ቀድም ብሎ ስራቸውን ማቆማቸውና ለዚህም ዋናው ምክንያት ወጣቶቹ ለስራው የተደራጁት ባህሪ ለባህሪ የሚተዋወቁ በራሳቸው ተነሳሽነት ሳይሆን በወረዳው በሚገኙ በሚመለከታቸው አመራሮች ጫና ባህሪ ለባህሪ የማይተዋወቁ 30

ወጣቶች ተደራጅተው ብድር ወስደው ስራ እንዲጀምሩ መደረጋቸው እንደሆነ የሚመለከታቸው የወረዳው ኃላፊዎችና ባለሙያዎች የገለጹ መሆናቸው፡፡

- ✓ በየካ ክ/ከተማ በወረዳ 10 እየሰሩ የሚገኙ አዲስአለም ወሰኔና ጓደኞቹ ቆዳና የቆዳ ውጤቶች ምርት ስራ ኢንትርፕራይዝ ተደራጅተው ብድር የወሰዱ የወጣቶች ብዛት 5 ሲሆን አሁን በስራው ላይ የሚገኝ 1 ብቻ መሆኑና 4 ስራ ላይ የሌሉ መሆናቸው፡፡

- ተደራጅተው ብድር የወሰዱ ኢንትርፕራይዞች በመንግስት ምን ምን ድጋፍ እንደሚደረግላቸው በግልጽ ያልተቀመጠ በመሆኑ፡-
  - ✓ በትግራይና አማራ ክልሎች ብድር ወስደው ወደ ስራ ከገቡ ኢንትርፕራይዞች መካከል ከወሰዱት ብድር የመስሪያ ቦታ /ሼድ/ በራሳቸው ወጪ በመገንባታቸው እና የጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንትርፕራይዝ ልማት ጽ/ቤቶች ወጣቶቹ ለመስሪያ ቦታ /ሼድ/ ለመገንባት ያወጡትን ወጪ ያልመለሱላቸው በመሆኑ፤ በገንዘብ እጥረት ምክንያት ወደ ስራ ለመግባት ባለመቻላቸው እንዲሁም ምርት አምርተው በመሸጥና ትርፋማ በመሆን የወሰዱትን ብድር ባለመመለሳቸው ለባንክ ወለድ ዕዳ እየተዳረጉና እየተበታተኑ ያሉ ኢንትርፕራይዞች መኖራቸው ከአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት ከተገኘው የሰነድ ማስረጃ ለመረዳት ተችሏል፤
  - ✓ እንዲሁም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ብድር ወስደው ወደ ስራ ከገቡ ኢንትርፕራይዞች ወስጥ ብድር ከመውሰዳቸው በፊት የመስሪያ ቦታ /ሼድ/ እንዲያገኙ ባለመደረጉ ለከፍተኛ ኪራይ እየተዳረጉ መሆናቸው ለምሳሌ በጉለሌ ክ/ከተማ ወረዳ 10 የሚገኝ ንስር የፈሳሽ ሳሙናና ጓደኞቹ ኢንትርፕራይዝ በወር ብር 12,000 እንዲከፍሉ ከመደረጉም በተጨማሪ ቦታው ለስራው የማይመች እና ጠባብ መሆኑ፣ በጉለሌ ክ/ከተማ ወረዳ 10 የሚገኝ ጥጋቤ ትሪንግ እና ጓደኞቹ ብረታብረት ስራ ኢንትርፕራይዝ በወር ብር 2,500 አንዲከፍሉ ከመደረጉም በተጨማሪ የመስሪያ ቦታው ከጣራ በስተቀር በሦስትም ጎኑ ግድግዳ የሌለው በመሆኑ የኢንትርፕራይዙ የስራ ማሽኖች፣ የተሰሩ ንብረቶች እና የስራ ግብአት የሆኑ የተለያዩ ብረቶች ለብክነትና ለስርቆት የተዳረጉ መሆናቸው፣

Figure 1:- በጉለሌ ክ/ከተማ ወረዳ 10 የሚገኝ ጥጋቤ ትሪንግ እና ጓደኞቹ ብረታብረት ስራ ኢንትርፕራይዝ

ታሕሳስ 2011 ዓ/ም

Figure 2:- በጉለሌ ክ/ከተማ ወረዳ 10 የሚገኝ ንስር የፈሳሽ ሳሙናና ጓደኞቹ ኢንትርፕራይዝ ታሕሳስ 2010 ዓ/ም

- *መብራት፣ ውኃ፣ መንገድ እና የመሳሰሉትን ለማሟላት የሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ግልጽና አስገዳጅ የሆነ አንቀጽ በማካተት መመሪያው ሊዘጋጅ እና ተግባራዊ ሊደረግ ባለመቻሉ፡-*
  - ✓ *በትግራይ ፣ ኦሮሚያ፣ አማራ፣ ሀረሪ ክልሎች እና በድሬደዋ መስተዳድር ብድር ወስደው ወደ ስራ ከገቡ ኢንትርፕራይዞች መካከል በመብራት፣ በውኃ፣ መንገድ*

እና በመሳሰሉት ችግሮች ምክንያት የሚጠበቅባቸውን ምርት በማምረትና በመሸጥ እዳቸውን ለመክፈል መቸገራቸውና በዚህ ምክንያት ስራ ሳይጀምሩ የተበታተኑ ኢንትርፕራይዞች መኖራቸው በኦዲቱ ወቅት ከተደረጉ ቃለ መጠይቆችና ከተሰበሰቡ የሰነድ ማስረጃዎች እና ምልከታ ለመረዳት ተችሏል፤

-

Figure 3:-**ተክሊትና ዘምካኤል ብሎኬት አምራች ሕ/ስ/ማህበር፣ ሙልጌታና ተስፋይ ከብት ማደለብ ሕ/ስ/ማህበር በደደቢት ማይክሮ ፋይናንስ ኩሓ ቅርንጫፍ በመሰረተ ልማት ችግር ምክንያት ስራ ያቋረጡ ኢንትርፕራይዞች**

- የሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ብድር ወስደው ወደ ስራ ገብተው ምርት ለሚያመርቱ ኢንትርፕራይዞች የገበያ ትስስር ስራ ለመፍጠር የሚያስችል አሰራር በመመሪያ እንዲወጣ ባለማድረጋቸው፡-
  - ✓ በትግራይ ፣ ኦሮሚያ እና አማራ ክልሎች እንዲሁም በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ብድር ወስደው ወደ ስራ ከገቡ ኢንትርፕራይዞች መካከል የሚጠበቅባቸውን ምርት ቢያመርቱም የገበያ ትስስር ያልተፈጠረላቸው በመሆኑ በገበያ እጦት ምክንያት እዳቸውን ለመክፈል እና ስራውን ውጤታማ ለማድረግ በመቸገራቸው ምክንያት ተስፋ ቆርጠው ኢንትርፕራይዞች መበታተናቸው፤

ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመመካከር ደንቦችና ሁኔታዎችን መወሰኑን በተመለከተ

38. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ባንኩ የፈንዱን ገንዘብ በአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት በኩል ለተጠቃሚዎች የሚያስተላልፍበትን ደንቦችና ሁኔታዎች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመመካከር ሊወስን እንደሚገባ የኢትዮጵያ ወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 995/2009 አ.ም በአንቀፅ 9 ንኡስ አንቀፅ 2 ተደንግጓል፡፡

39. ይሁን እንጂ ጉዳዩን አስመልክቶ የኦዲት ቡድኑ ባካሄዳቸው የዶክመንት ክለሳዎች እና ከሚመለከታቸው የሚንስቴር መስሪያ ቤቱ የስራ ሃላፊዎች፣ የንግድ ባንክ የስራ ሃላፊወች፣ እና የክልል የፋይናንስ ቢሮ የስራ ሃላፊዎች ጋር ባካሄዳቸው ቃለመጠይቆች መሰረት ለወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ ከተመደበው 10 ቢለዮን ብር ውስጥ እስከ ጥር 2011 ዓ/ም ወደ 9.1 ቢሊዮን ብር ወጪ ሆኖ ለተጠቃሚዎች ቢሰራጭም ረቂቅ ሪፖርቱ እስከተላከበት ጊዜ ድረስ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ባንኩ የፈንዱን ገንዘብ በአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት በኩል ለተጠቃሚዎች የሚያስተላልፍበትን ደንቦችና ሁኔታዎች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመመካከር ያልወሰነና በስራ ላይ እንዲውል ያላደረገና በአዋጁ የተሰጠውን ሃላፊነት እንዳልተወጣ በኦዲቱ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

40. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች ለኦዲቱ ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እና በኦዲቱ መውጫ ስብሰባ በሰጡት መልስ፣ መ/ቤታቸው በወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ አዋጅ ቁጥር 995/2009 ዓ/ም አንቀጽ 9/2 እንዲሁም የኢትዮጵያ ወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ ለማስተዳደር በደብዳቤ ቁጥር ማኢ-30/19/12 በቀን 01/10/2009 ዓ/ም በገንዘብ ሚኒስቴር ፣ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና የየክልሎቹ የፋይናንስ ቢሮዎች ጋር በተደረገው የመግባቢያ ስምምነት **አንቀጽ** 3/3 **እና** 4/1 መሰረት የፈንዱ ገንዘብ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት የሚተላለፍበትን ደንቦችና ሁኔታዎች ለክልሉ ፋይናንስ ቢሮ እንዲያሳውቅና የክልሉ ፋይናንስ ቢሮ የፈንዱን ገንዘብ መ/ቤታቸው በወሰነው የማበደሪያ ደንቦችና ሁኔታዎች ለተጠቃሚዎች እንዲያስተላልፍ በተጣለው ግዴታ መሰረት መ/ቤታቸው የብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የፋይናንስ ቢሮዎች ለአነስተኛና የፋይናንስ ተቋማት የፈንዱን ገንዘብ የሚያስተላልፍበትን ደንብና ሁኔታዎች የሚወሰንና በእያንዳንዱ ክልል የፋይናንስ ቢሮና አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማቱ መካከል ሊደረግ የሚገባ ሞዴል የገንዘብ

አስተዳደር ውል በማዘጋጀት ለእያንዳንዱ ክልል የፋይናንስ ቢሮ መስጠቱ፣ የውሉ ማስረጃ ከዚህ ደብዳቤ ጋር በአባሪ ያያያዙ መሆናቸው ገልጸዋል፡፡

41.በመሆኑም ከላይ በተገለጸው ሰነድ በተወሰነው የማበደሪያ ደንቦችና ሁኔታዎች መሰረት የዘጠኙ ክልሎች ፣ የአዲስ አበባና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮዎች ገንዘቡን ለተጠቃሚዎች ማስተላለፍና ማስተዳደር ያለባቸው በመሆኑና በዚሁ መሰረት የገንዘብ አስተዳደር ውሉን ከፈንዱ ተጠቃሚዎች ጋር ያደረጉ ስለሆነ በዚህ ውል መሰረት ያለባቸውን ግዴታ ባለመወጣታቸው መተቸት ያለባቸው የክልልና የከተማ አስተዳደሮች የፋይናንስ ቢሮዎች እንጂ መ/ቤታቸው ሊሆን እንደማይገባ ገልጸዋል፡፡

42.የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ይህንን ይበሉ እንጂ፣ የወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር995/2009 ዓ/ም መሰረት ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ባንኩ የፈንዱን ገንዘብ በአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት በኩል ለተጠቃሚዎች የሚያስተላልፍበትን ደንቦችና ሁኔታዎች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመመካከር እንደሚወስን በግልፅ የተደነገገ ሲሆን በዚህ አዋጅ ውስጥ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ይህን ሃላፊነቱን በመግባቢያ ሰነድ ወይም በሌላ ሁኔታ ለሌላ አካል አሳልፎ እንደሚሰጥ ያልተገለፀ በመሆኑ እንዲሁም ለአንድ ተቋም በአዋጅ የተሰጠ ሃላፊነት የሚቀየረው በአዋጅ እንጂ ከሌሎች ተቋማት ጋር በሚደረግ የመግባቢያ ሰነድ ባለመሆኑ እንዲሁም የተጠቀሰው የመግባቢያ ሰነድ ህጋዊነት የሌለው በመሆኑ፣ በተጨማሪ የጸደቀና ስራ ላይ እንዲውል የተደረጉ ደንቦችና ሁኔታዎች አለመኖራቸው በቀን 26/11/2010 ዓ/ም የሚመለከታቸው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች በተደረገላቸው ቃለ መጠይቅ የገለጹ በመሆናቸው፣ ለነባራዊ ሁኔታ እና ከተሰጠው ምላሽ ጋር የሚቃረን በመሆኑ እንዲሁም ተግባራዊ እንዲደረግ ለክልሎች ሆነ ለባንኩ የተላከ ማህተምና የደብዳቤ ቁጥር ያሟላ ደንብና ሁኔታ ያለው ሰነድ ለኦዲቱ ያልቀረበ በመሆኑ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ሃላፊ የተሰጠው መልስ በኦዲቱ ተቀባይነት የለውም፡፡

43.በአዋጅ በተሰጠው ኃላፊነት መሰረት ሚኒስቴር መ/ቤቱ ባንኩ የፈንዱን ገንዘብ በአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት በኩል ለተጠቃሚዎች የሚያስተላልፍበትን ደንቦችና ሁኔታዎች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመመካከር ባለመወሰኑና አስጽድቆ ህጋዊ በሆነ ደብዳቤ ባንኩ ወይም ባንኩ ለወከላቸው የክልልና የከተማ መስተዳድር ፋይናንስ ቢሮዎች ስራ

ላይ እንዲያወሉት አቅጣጫ ባለመስጠቱ ምክንያት ከ9 ቢሊዮን ብር በላይ የፈንዱን ገንዘብ አዋጁ ስልጣን ባልሰጣቸው በየክልሉ በሚገኙ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት በተዘጋጁ ወጥነት በሌላቸው የተለያዩ ደንቦችና ሁኔታዎች ወጪ ተደርጎ ለተጠቃሚዎች መሰራጨቱን ቀጥለው በተዘረዘሩ ነጥቦች ለመረዳት ተችሏል፡፡

- የገንዘብ ሚኒስቴር ባንኩ የፈንዱን ገንዘብ በአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት በኩል ለተጠቃሚዎች የሚያስተላልፍበትን ደንቦችና ሁኔታዎች አዘጋጅቶና አጽድቆ ስራ ላይ እንዲያውሉት ባለመላኩ ቀጥለው በተዘረዘሩ በአዋጁ ከተገለጸው ውጪ በራሳቸው ባዘጋጇቸው ደንቦችና መመሪያዎች እንደ ደንብ ተጠቅመው ገንዘቡ ለተጠቃሚዎች ማስተላለፋቸው የአማራ፣ የደደቢት፣ የኦሮሚያ፣ የሀረር፣ የድሬ እና የአዲስ ብድርና ቁጠባ ተቋማት አ/ማህበር የሚመለከታቸው ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች የኦዲት ቡድኑ ላቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በማስረጃ በማስደገፍ ገልጸዋል፡፡እነሱም፡-ስልጣን በሌላቸው በተለያዩ አካላት የተዘጋጁ እና ስራ ላይ የዋሉ እንደ ደንብ ሆነው ያገለገሉ መመሪያዎች-
    - ✓ የኦሮሚያ ብድርና ቁጠባ ተቋም የወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ ደንብ በመጋቢት 2009 ዓ/ም አዲስ አበባ ፊንፍኔ፣
    - ✓ በአዲስ የብድርና ቁጠባ ተቋም አ.ማ የወጣቶች ተዘዋዋሪ ብድር ፖሊሲ የካቲት 2009 ዓ/ም አዲ/ብ/ቁ/ተ-አዲስ አበባ፣
    - ✓ ደደቢት ብድርና ቁጠባ ተቋም አ.ማ ጥር 2009 ዓ/ም በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የተዘጋጀ የኢትዮጵያ ወጣቶች የዕድገትና የልማት ፓኬጅ የወጣቶች የተዘዋዋሪ ብድር ፈንድ አስተዳደር መመሪያ በክልላቸው ቋንቋ በመተርጎም በገጠር እና በከተማ ለሚገኙ ወጣቶች ከደደቢት ማይክሮ ፋይናንስ ሊያገኙ የሚችሉት አማራጮችና አገልግሎት የፋይናንስ እና የብድር መመሪያ መጋቢት 2009 ዓ/ም መቐለ የተዘጋጀ፣
    - ✓ የድሬ ብድርና ቁጠባ ተቋም የወጣቶች ተዘዋዋሪ ብድር አፈጻጸም መመሪያ መጋቢት 2009 ዓ/ም፣
    - ✓ የሀረር ብድርና ቁጠባ ተቋም ቢሔራዊ ባንክ የተዘጋጀ ህጋዊነት የሌለው የወጣቶች የተዘዋዋሪ ብድር ፈንድ አስተዳደር መመሪያ እንደሚጠቀሙ ገልጸዋል፡፡

- ✓ የአማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም የክልሉ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ፣ የክልሉ የቴክኒክ እና ሙያ ኢንርፕራይዞች ቢሮ፣ የክልሉ የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮ እንዲሁም ከተቋማቸው ጋር በመወያየት መጋቢት 2009 ዓ/ም የብድሩ መመሪያ በማዘጋጀት እና በክልሉ መንግስት እንዲጸድቅ በማድረግ ስራ ላይ እንዲውል ማድረጋቸው ለኦዲቱ ከቀረቡ የሰነድ ማስረጃዎች እና ለቃለ መጠይቆች ከተሰጠው ምላሽ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

44.በተጨማሪ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመመካከር የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የፈንዱን ገንዘብ በአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት በኩል ለተጠቃሚዎች የሚያስተላልፍበትን ወጥና ህጋዊ እውቅና ያላቸው ደንቦችና ሁኔታዎች ባለማዘጋጀቱ በቀጥታ የፈንዱ ተጠቃሚ በሆኑ የኢትዮጵያ ወጣቶች ላይ ቀጥለው የተዘረዘሩ ችግሮች የፈጠረ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ከተደረጉ ቃለ መጠይቆችና ከተሰበሰቡ ማስረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡-

- ተደራጅተው ከተዘዋዋሪ ብድር ፈንድ ብድር የሚጠይቁ ወጣቶች ለስራው ከሚያስፈልጋቸው የብር መጠን ውስጥ ቀድመው 10% መቆጠብ እንዳለባቸው የሚገልጽ ህጋዊ የሆነ ደንብና ሁኔታ በሌለበት ቀድመው ቁጠባውን ማሟላት ባልቻሉ ላይ ቀጥለው የተገለጹት ችግሮች በኦዲቱ ወቅት ታይቷል፡-

  በናሙና በታዩ በትግራይ፣ ኦሮሚያ እና አማራ ክልሎች እንዲሁም በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር የሚገኙ ቀድሞ ለመቆጠብ አቅም የሌላቸው ወጣች ፡-

  - ✓ ለስራው የሚያስፈልጋቸውና ለሚበደሩት የብር መጠን 10% መቆጠብ ያልቻሉ የፈንዱ ተጠቃሚዎች እንዳይሆኑ መደረጉ፤

45.እንዲሁም በተዘዋዋሪ ብድር ፈንድ ተጠቃሚ የሆኑ ወጣቶች /ኢንትርፕራይዞች/ ተመላሽ የተደረገ ገንዘብ እንዴትና በምን መልኩ መልሶ ስራ ላይ መዋል እንዳለበት በግልጽ የተቀመጠ ነገር ባለመኖሩ የደደቢት ማይክሮ ፋይናንስ ተቋም አ/ማህበር፣ የአዲስ ብድርና ቁጠባ ተቋም አ/ማህበር፣ የአማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም አ/ማህበር እና የኦሮሚያ ብድርና ቁጠባ አ/ማህበር ከተሰጠው ብድር ተመላሽ የተደረገ የፈንዱ ገንዘብ እንዴት መልሰው መጠቀም እንዳለባቸው መቸገራቸውን በኦዲቱ ወቅት በተደረገው ቃለ መጠይቅ ገልጸዋል፡፡

የሚኒስቴር መ/ቤቱ አደረጃጀት እና የመረጃ ልውውጥ ስርአትን በተመለከተ

46.ሚኒስቴር መ/ቤቱ የወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድን በተመለከተ በአዋጅ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት ለመወጣት የሚያስችል አደረጃጀት እና የመረጃ ልውውጥ ስርአት በመዘርጋት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

47.ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአዋጅ የተሰጠውን የወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ ተግባርና ኃላፊነት ለመወጣት የሚያስችል ነባር አደረጃጀት እና የመረጃ ልውውጥ ስርአት እንዳለው በቀን 26/11/2010 ዓ/ም ለሚመለከታቸው የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በቀረበ ቃለ መጠይቅ በማስረጃ በማስደገፍ ገልጸዋል፡፡ ለምሳሌ የህግ አገልግሎት ዳይሪክቶሬት መመሪያ፣ ደንቦች እና ሁኔታዎች ለማውጣት፣ የፊሲካል ፖሊሲ ዳይሬክቶሬት ለፈንዱ የተመደበ 10 ቢሊዮን ብር ክልሎች ባላቸው የወጣቶች ብዛት መሰረት የማከፋፈል እንዲሁም የመንግስት ሂሳብ ዳይሪክቶሬት የተመረመረ የፈንዱን ሂሳብ ከሚመለከታቸው አካላት በአዋጁ በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት የመሰብሰብ ስራ እንደሚሰሩ በማስረጃ በማስደገፍ ገልጸዋል፡፡

48.ሆኖም ከፊሲካል ፖሊሲ ዳይሬክቶሬት በክልሎች እና በከተማ መስተዳደር የሚገኙ ወጣቶች ብዛት መሰረት በማድረግ ከጠቅላላ የፈንዱ ገንዘብ 10 ቢሊዮን ብር ውስጥ 5 ቢሊዮን ብር ያላቸውን ድርሻ ለንግድ ባንክ ከማሳወቁ በስተቀር ህግ አገልግሎት ዳይሪክቶሬት የፈንዱ ገንዘብ ከ90% በላይ ወጪ እስከ ሆነበት ቀን ድረስ ፈንዱን ውጤታማ ሊያደርጉ የሚያስችሉ መመሪያ ፣ ደንቦች እና ሁኔታዎች ያላወጣ መሆኑ እንዲሁም የመንግስት ሂሳብ ዳይሪክቶሬት የተመረመረ የፈንዱን ሂሳብ ከሚመለከታቸው ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ወይም ባንኩ ከወከላቸው የክልልና የከተማ መስተዳድር የፋይናንስ ቢሮዎች በአዋጁ በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት የተመረመሩ የፈንዱን ገንዘብ አፈጻጸም ሪፖርቶች /መረጃ/ የመሰብሰብ እና መረጃ የመለዋወጥ ስራ እንዳልሰራ በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

49.ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች ለኦዲቱ ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት መልስ፤ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአዋጅ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት ለመወጣት የሚያስችል አደረጃጀት እና የመረጃ ልውውጥ ስርአት በመዘርጋት ተግባራዊ ማደረጉንና አለማድረጉን በተመለከተ ምላሽ አልተሰጠም፡፡

50. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ አፈጻጸም ውጤታማ ለማድረግ እና በአዋጅ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት ለመወጣት የሚያስችል አደረጃጀት እና የመረጃ ልውውጥ ስርአት ቢኖረውም የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት ባለመወጣቱ ምክንያት ለተዘዋዋሪ ብድር ፈንድ ከተመደበው 10 ቢሊዮን ብድር ውስጥ ከ9.1 ቢሊዮን ብር በላይ ወጪ ሆኑ ለተጠቃሚዎች ሲሰራጭ፡-

- ፈንዱ የሚተዳደርበት ደንብና መመሪያ አላዘጋጀም፣
- እንዲሁም እስከ ሰኔ 2010 ዓ/ም ወጪ የሆነው የፈንዱ ገንዘብ የ2009 እና የ2010 በጀት አመት የተመረመረ ሂሳብ ለሚኒስትሮች እና ለተወካዮች ምክርቤት ሪፖርት አላቀረበም፤

ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፈንዱን አጠቃቀም ሪፖርት ማቅረቡን በተመለከተ

51. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከባንክ የሚደርሰውን የፈንዱን አጠቃቀም መግለጫና ሪፖርት በተጠቃለለው ዓመታዊ የመንግስት ሂሣብ ሪፖርት ውስጥ በማካተት በየደረጃው ለሚኒስትሮች ምክር ቤት እና ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሊያቀርብ ይገባል፡፡

52. ይሁን እንጂ የኦዲት ቡድኑ ጉዳዩን አስመልክቶ ባካሄዳቸው የዶክሜንት ክለሳ እና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ከሚኒስቴር መስሪያቤቱ የስራ ሃላፊዎች፤ከንግድ ባንክ የስራ ሃላፊዎች፤እና ከክልል መስተዳድር የፋይናንስ ቢሮዎች የስራ ሃላፊዎች ጋር ባካሄዳቸው ቃለመጠይቆች መሰረት ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከ2009 ዓ/ም እስከ በ2010 ዓ/ም የፈንዱን ገንዘብ ከ80 % በላይ ከመንግስት ካዝና ወጪ ሆኖ የተሰራጨ ቢሆንም ከባንክ ወይም ባንኩ በአዋጅ ከተገለፀው ውጭ ከወከላቸው ዘጠኙ ክልሎች እና ሁለቱ የከተማ መስተዳድር የፋይናንስ ቢሮዎች የፈንዱን አጠቃቀም የሚያሳይ የተመረመረ ሪፖርት እንዳልደረሰው እንዲሁም ፤የክልሎቹን እና የከተማ መስተዳድር የፋይናንስ ቢሮዎችን ሪፖርት መሰረት ያደረገ የተመረመረ የሂሳብ መግለጫ ሪፖርት በየደረጃው ለሚኒስትሮች ምክር ቤት እና ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እያቀረበ አለመሆኑን በኦዲት ወቅት ለማረጋገጥ ተችላል፡፡

53. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከ2009 ዓ/ም እስከ በ2010 ዓ/ም የፈንዱን ገንዘብ ከ80 % በላይ ከመንግስት ካዝና ወጪ ሆኖ የተሰራጨ ቢሆንም ከባንክ ወይም ባንኩ በአዋጅ ከተገለፀው ውጭ ከወከላቸው ዘጠኙ ክልሎች እና ሁለቱ የከተማ መስተዳድር የፋይናንስ ቢሮዎች

የፈንዱን አጠቃቀም የሚያሳይ የተመረመረ ሪፖርት እንዳልደረሰው ፤የክልሎቹን እና የከተማ መስተዳድር የፋይናንስ ቢሮዎችን ሪፖርት መሰረት ያደረገ የተመረመረ የሂሳብ መግለጫ ሪፖርት በየደረጃው ለሚኒስትሮች ምክር ቤት እና ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እያቀረበ አለመሆኑን ከቀረቡልን የሰነድ ማስረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

54.ሆኖም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከባንክ ወይም ባንኩ በአዋጅ ከተገለፀው ውጭ ከወከላቸው ዘጠኙ ክልሎች እና ሁለቱ የከተማ መስተዳድር የፋይናንስ ቢሮዎች የፈንዱን አጠቃቀም የሚያሳይ መግለጫና ሪፖርት ያልደረሰው ሲሆን፤ የፈንዱን ገንዘብ ስርጭት ወይም ወጪ መደረጉን ብቻ በሚያሳይ ሁኔታ በተጠቃለለው ዓመታዊ የመንግስት ሂሣብ ሪፖርት ውስጥ በተሰብሳቢ የሂሳብ መደብ በብድር የተሰጠ መሆኑን በሚያሳይ መልኩ ሳይሆን **በሂሳብ መደብ** 6412 Grants, Contribution, and Subsidies to institutions and enterprises ለክልሎች ድጎማ እንደተሰጠ በሚያሳይ መልኩ በማካተት በ2009 እና በ2010 በጀት ዓመት ሪፖርት መደረጉ ከቀረቡልን የሰነድ ማስረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡እንዲሁም፤

- ✓ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ፣ የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት መስተዳድር የገ/የኢኮ/ትብብር ቢሮ በቅደም ተከተል ከአዲስ ብድርና ቁጠባ ተቋም አ/ማህበር እና ከኦሮሚያ ብድርና ቁጠባ ተቋም አ/ማህበር በየስድስት ወሩ የ2009 ዓ/ም እና የ2010 ዓ/ም የፈንዱን የገንዘብ አጠቃቀም የሚያሳይ ሪፖርት ያልተላከላቸው መሆኑ፣
- ✓ በሌላ በኩል ውክልና የሰጣቸው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በውክልናው መሰረት የተመረመረ የፈንዱን ሂሳብ ከተሰጠው የኦዲት አስተያየት ጋር በፌደራል መንግስት የበጀት አመት መሰረት ለገንዘብ ሚኒስቴር ይህ ሪፖርት እስከተዘጋጀበት ጊዜ ድረስ ያልላኩ ሲሆን፤ ሆኖም ተጨማሪ ገንዘብ ሲያስፈልጋቸው እና ሲጠይቁ ቀድሞ የወሰዱትን ገንዘብ ለወጣቶች /ለኢንትርፕራይዞች/ ስለመሰራጨቱ ብቻ የሚሳይ በደብዳቤ የሚያሳወቁ መሆኑን የሚመለከታቸው የቢሮ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች የኦዲት ቡድኑ ባደረገላቸው ቃለ መጠይቅ የሰነድ ማስረጃዎችን በማስደገፍ ገልጸዋል፡፡

55.ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች ለኦዲቱ ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት መልስ፤ የፈንዱ ገንዘብ ተመላሽ በሚደረግ /ብድር/ ሂሳብ መደብ መመዝገብ ሲገባ

ለክልሎች ድጋፍ እንደተሰጠ በሚያሳይ ሂሳብ መደብ የተመዘገበውን በተመለከተ የፌንዱ ገንዘብ በበጀት ሲታወጅ በሂሳብ መደብ 6412 ስለታወጀ በጀቱ በታወጀበት ሂሳብ መደብ ለክልሎች ተላልፎ ስለተመዘገበ እንደሆነ፣ ነገር ግን ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ወይም ባንኩ ውክልና ከሰጣቸው የክልል ፋይናንስ ቢሮዎች የተመረመረ የፌንዱ አጠቃቀም መግለጫ እና ሪፖርት ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና ለሚኒስትሮች ምክር ቤት በኦዲቱ እንደተገለጸው ሪፖርት አለማቅረባቸውንና እንደ ክፍተት እንደሚቀበሉት ገልጸዋል፡፡

56.ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከባንኩ የሚደርሰውን የፌንዱን አጠቃቀም መግለጫና ሪፖርት መሰረት በተጠቃለለው ዓመታዊ የመንግስት ሂሣብ ሪፖርት ውስጥ በማካተት በየደረጃው ለሚኒስትሮች ምክር ቤት እና ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲቀርብ ባለማድረጉ በኦዲት ሪፖርቱ በሁሉም መመዘኛ መስፈርቶች በፌንዱ አፈጻጸም ዙርያ የታዩ ችግሮች በወቅቱ በሚመለከታቸው የመንግስት የበላይ አመራሮች ውይይት ተደርጎባቸው የሚሻሻሉበት የመፍትሄ አቅጣጫ እንዳይቀመጥላቸው በማድረጉ ችግሮቹ ከአመት ወደ አመት እየተባባሱ በብድር መልክ ከፌንዱ ለወጣቶች የተሰጠው ገንዘብ የመመለስ ዕድሉ እንዲጠብ ያደርጋል፡፡

ሚንስቴር መ/ቤቱ የየክልሎችን የፌንድ ድርሻ በማስላት ማሳወቁን በተመለከተ

57.ሚኒስቴር መ/ቤቱ የየክልሉን ወጣቶች ቁጥር መሠረት በማድረግ ከፌንዱ ገንዘብ ላይ ለየክልሉ ሊከፋፈል የሚገባውን ድርሻ በማስላት ለባንኩ ሊያሳውቅ ይገባል፡፡

58.ሚኒስቴር መ/ቤቱ የየክልሎቹን ወጣቶች ቁጥር መሠረት በማድረግ ከፌንዱ ገንዘብ ላይ ለየክልሉ ሊከፋፈል የሚገባውን ድርሻ በማስላት በአዋጅ ስልጣን ለተሰጠው ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በቁጥር ማኢ-30/19/10 በቀን 14/06/09 ዓ/ም ማሳወቁ፣ የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ በጥር 29/2009 ዓ/ም በደብዳቤ ቁጥር መገ-11885 በክልሎችና በሁለቱም ከተማ መስተዳድሮች የሚገኙ ዕድሚያቸው ከ18-34 የሚገኙ የወጣቶች ብዛት/ቁጥር/ ትንበያ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ በላከው ሰነድ መሰረት ክልሎችና ከተማ መስተዳድሮች ከ5 ቢሊዮን ብር ያላቸውን ድርሻ እንዲያውቁት የተደረገ መሆኑን ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ትሬዠሪ ዳይሪክቶሬት በሐምሌ 10 ቀን 2010 ዓ/ም ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የመንግስት ሂሳብ ዳይሪክቶሬት ከተላከ የውስጥ ማስታወሻ ለመረዳት ተችሏል፡፡

59.የክፍፍሉ ዝርዝር እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡ ጠቅላላ ዕድሚያቸው ከ18-34 በክልሎች ውስጥ የሚገኙ የኢትዮጵያ ወጣቶች ብዛት 29,975,956 መሆኑን፡፡ እነዚህም፡-

60.በትግራይ፣ አፋር፣ አማራ፣ ኦሮሚያ፣ ሶማሊያ፣ ቤንሻንጉል ጉሙዝ፣ ደቡብ ብሔር ብሄረሰቦች እና ህዝቦች፣ ጋምቤላ፣ ሀረሪ፣ አዲስ አበባና ድሬደዋ በቅደም ተከተል ያላቸው የወጣት ብዛት፡- 1,578,463፣ 618,827፣ 8,024,773፣ 10,314,270፣ 1,806,539፣ 338,433፣ 5,643,731፣ 150,41፣ 80,259፣ 1,255,486 እና 164,762 ሲሆን ለፈንዱ ከተፈቀደው 10 ቢሊዮን ብር ፈንድ ውስጥ 5 ቢለዮን ብር ለክልሎች የተከፋፈለው /የተመደበላቸው/ የገንዘብ መጠን በቅደም ተከተል ብር 263,288,174.59፣ 103,220,557.73፣ 1,338,534,913.16፣ 1,720,423,804.98፣ 301,331,330.31፣ 56,450,741.51፣ 941,376,283.67፣ 25,089,107.25፣ 13,387,228.97፣ 209,4415,499.23፣ እና 27,482,358.61 የተከፋፈለ መሆኑን፤ ነገር ግን ለፈንዱ ከተመደበው 10 ቢሊዮን ብር ወስጥ ከ9.1 ቢለዮን ብር ወጪ ሆኖ ለክልሎች የተሰራጨ ቢሆንም የክልሎች ድርሻ ባንኩ እንዲያውቀው የተደረገው የ5 ቢሊዮን ብር ብቻ ስለሆነ ከተከፋፈለው 4.1 ቢሊዮን የፈንዱ ገንዘብ የክልሎች ድርሻ የማሳወቅ ስራ ባልተሰራበት ሁኔታ ለክልሎች እንዲከፋፈል መደረጉ ለኦዲቱ ከቀረቡ ሰነዶች ለመረዳት ተችሏል፡፡

61.ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች ለኦዲቱ ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት መልስ፤ ነባራዊ ሁኔታዎች መግለጫ ተራ ቁጥር 4 /ገጽ 11/ ላይ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የየክልሎቹን ወጣቶች ቁጥር መሰረት በማድረግ ከፈንዱ ገንዘብ ላይ ለየክልሉ ሊከፋፈል የሚገባውን ድርሻ በማስላት ለባንኩ ማሳወቃቸው የሚገልጽ በማስረጃ በማስደገፍ አቅርቧል፡፡

62.ለወጣቶች ፈንድ ሊከፋፈል የሚገባውን ድርሻ ለባንኩ ያለማሳወቅ በተመለከተ ለወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ ብድር ዓላማ የሚውለውን ድርሻ ለባንኩ የማሳወቅ ስራ በመንግስት በተወሰነው እና በተፈረመው የሶስትዮሽ የመግባቢያ ሰነድ የተሻሻለ ስለመሆኑ በመግለጽ፤ ከጠቅላይ ሚ/ር ጽ/ቤት ታህሳስ 11 ቀን 2011 ዓ/ም. በቁጥር መ90-7/4/1 የተጻፈ ደብዳቤ ኮፒ 1 ገጽ ለግንዛቤ ይረዳ ዘንድ ከዚሁ ጋር አያይዘው አቅርበዋል፡፡

63.እንዲሁም የሚመለከታቸው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በኦዲት መውጫ ስብሰባ በሰጡት ምላሽ በወቅቱ መንግስት ለወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ የመደበው 10 ቢሊዮን ብር በሁለት ጊዜ እንዲከፈል በወሰነው መሰረት የመጀመሪያው 5 ቢሊዮን ብር

ክፍያ የክልሎች ወጣት ቁጥር መሰረት በማድረግ ያላቸውን ድርሻ ለባንክ ማሳወቃቸው፤ ለሁለተኛ ጊዜ የተደረገው ክፍያ ክልሎች ያላቸውን ድርሻ መጀመሪያ እንዲያውቁት በተደረገው መሰረት ድርሻቸውን ያውቃሉ በሚል ታሳቢ በማድረግ ያላሳወቁ መሆናቸው ለወደፊቱ ግን ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት የክልሎች ከፈንዱ ያላቸው ድርሻ እንዲያውቁት እንደሚደረግ ገልጸዋል፡፡

64.የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ይህንን ይበሉ እንጂ፤

- ነገር ግን ከተመደበው 10 ቢሊዮን ብር ወስጥ ከ9.1 ቢለዮን ብር ወጪ ሆኖ ለክልሎች የተሰራጨ ቢሆንም የክልሎች ድርሻ ባንኩ እንዲያውቀው የተደረገው የ5 ቢሊዮን ብር ብቻ ስለሆነ ከተከፋፈለው 4.1 ቢሊዮን የፈንዱ ገንዘብ የክልሎች ድርሻ የማሳወቅ ስራ ባልተሰራበት ሁኔታ ለክልሎች እንዲከፋፈል በመደረጉ የተሰጠው ምላሽ በከፊል ለኦዲቱ አጥጋቢ አይደለም፡፡
- እንዲሁም ለወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ ብድር ዓላማ የሚውለውን ድርሻ ለባንኩ የማሳወቅ ስራ በመንግስት በተወሰነው እና በተፈረመው የሶስትዮሽ የመግባቢያ ሰነድ የተሻሻለ ስለመሆኑ በመግለጽ፤ ከጠቅላይ ሚ/ር ጽ/ቤት ታህሳስ 11 ቀን 2011 ዓ/ም. በቁጥር መ90-7/4/1 የተጻፈ ደብዳቤ ኮፒ 1 ገጽ ለግንዛቤ ይረዳ ዘንድ ከዚሁ ጋር አያይዘው ቢሆንም፤
  - ✓ አንደኛ የወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ የመግባቢያ ስምምነቱ ሚኒስቴር መ/ቤቱ አጽድቆ ለክልል ፋይናንስ ቢሮዎች የላከው በሰኔ 01/2009 ዓ/ም በደብዳቤ ቁጠር ማኢ-30/19/12 ሲሆን የሶስትዮሽ የመግባቢያ ሰነድ እንዲሻሻል ከጠቅላይ ሚ/ር ጽ/ቤት የተጻፈው ታህሳስ 11 ቀን 2011 ዓ/ም በደብዳቤ ቁጥር መ90-714/1 በመሆኑ፤ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ስልጣን ሳይኖረው የክልል ፋይናንስ ቢሮዎች ከንግድ ባንክ የተቀበሉትን የውክልና ተግባራዊ እንዲያደርጉት አቅጣጫ /መመርያ የሰጠው ከጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት ከተላከው ደብዳቤ **ከአንድ አመት ከሰባት ወር** በፊት ቀድሞ በመሆኑ እና ከትእዛዝ በፊት ትግበራ የማይቀድም በመሆኑ በጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት ትእዛዝ መሰረት የተደረገ አለመሆኑ ከቀረቡ ሰነዶች ለመረዳት የተቻለ በመሆኑ፣

- ✓ እንዲሁም ሚኒስትሮች ምክር ቤት የወጣው ህግ የመተግበር እንጂ በአዋጅ የወጣ ህግ የመሻርም ሆነ የመቀየር ስልጣን የሌለው ከመሆኑም ባሻገር፤ የወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ አዋጁ በአዋጅ እስካልተሻረ፤ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በአዋጅ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት ለሌላ ሦስተኛ ወገን በውክልና የመስጠት ስልጣን የሌለው በመሆኑ፤ በአዋጁ መሰረት የገንዘብ ሚኒስቴርም ይህ ህጋዊ ያልሆነ የውክልና ውል ስራ ላይ እንዲውል ለክልል/ለከተማ መስተዳደር ፋይናንስ ቢሮዎች መመርያ ወይም አቅጣጫ የመስጠት ስልጣንም ሆነ ኃላፊነት የሊለው በመሆኑ፤ የኢትዮጵያ ወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ አዋጅ ቁጥር 995/09 ክፍል ሦስት አንቀጽ 16 ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች በሚለው ይህን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ በአዋጁ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት እንደማይኖው ብግልጽ ያስቀመጠ በመሆኑ ለነባራዊ ሁኔታው የተሰጠው ምላሽ ለኦዲቱ አጥጋቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

65. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የየክልሉን ወጣቶች ቁጥር መሠረት በማድረግ ከፈንዱ ገንዘብ ላይ ለየክልሉ ሊከፋፈል የሚገባውን ድርሻ በማስላት በወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ አዋጅ መሰረት ስልጣን ለተሰጠው ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ማሳወቅ ሲገባው በአዋጅ ከተገለጸው ውጭ ለክልሎች እና ለከተማ መስተዳድሮች ማሳወቁ፤ በመንግስት የወጣው አዋጅ እንዳይተገበርና ስራ ላይ እንዳይውል ከማደረጉም ባሻገር፤ በአዋጅ ስለጣን እና ኃላፊነት ያልተሰጣቸው አካላት ስራቸውን በሚሰሩበት ወቅት ለሚፈጽሟቸው ጉድለቶች ተጠያቂ ለማድረግ የሚደረገው ሂደት አስቸጋሪና የተወሳሰበ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከባንኩ በሚቀርብለት ጥያቄ መሠረት ከተጠቃለለው ፈንድ ላይ ክፍያ መፈጸሙን በተመለከተ

66. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6/2 መሠረት ከባንኩ በሚቀርብለት ጥያቄ መሠረት ከተጠቃለለው ፈንድ ላይ ክፍያ ሊፈጽም ይገባል፡፡

67. በወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ አዋጅ አንቀጽ 6/2 እና በአንቀጽ 7 እንደተቀመጠው ሚኒስቴር መ/ቤቱ ፈንዱን ለማስተዳደር በተሰየመው አካል /የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ/ በሚያቀርበው ጥያቄ መሰረት የፈንዱን ገንዘብ ከተጠቃለለው ፈንድ ውስጥ ማስተላለፍ እንዳለበት ያዛል፡፡

68.ሆኖም ሚኒስቴር መ/ቤቱ እስከ ጥር 2011 ዓ/ም ድረስ ፈንዱን የማስተዳደር ስልጣን ለተሰጠው ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሳይሆን አዋጁ በማይፈቅደው ባንኩ ውክልና ለሰጣቸው ዘጠኙ ክልሎች እና ሁለቱ ከተማ መስተዳድር የፋይናንስ ቢሮዎች ባቀረቡት ጥያቄ መሰረት ከተጠቃለለው ፈንድ ከ9 ብሊዮን ብር በላይ ክፍያ የፈጸመ መሆኑን ለሚመለከታቸው የገንዘብ ሚኒስቴር ኃላፊዎች፣ እንዲሁም ለትግራይ፣ አማራ፣ ኦሮሚያ ክልሎች እና ለአዲስ አበባ ከተማ ፋይናንስ ቢሮ ኃላፊዎች ከቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ እና በኦዲቱ ወቅት ከቀረቡ የሰነድ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

69.ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች ለኦዲቱ ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት መልስ፤ በአዋጁ አንቀጽ 6/2 መሰረት የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በሚያቀርበው ጥያቄ መሰረት ፈንዱን ማስተላለፍ በተመለከተ አሰራሩ በመንግስት ውሳኔ ተቀይሮ በተፈረመው የመግባቢያ ሠነድ አንቀጽ 3/4 መሰረት መፈጸሙን፤ ነገር ግን በወቅቱ የነበረው ሁኔታ የፈጠረው በመሆኑ እና ከምክትል ጠቅላይ ሚኒስቴር ቢሮ በተሰጠው ትዕዛዝ መሰረት በዚሁ መልክ ሊሰራ መቻሉ ሆኖም በኦዲቱ የተገለጸው ትክክል መሆኑን ገልፀዋል፡፡

70.የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ይህንን ይበሉ እንጂ፤ አንድ አዋጅ የሚቀየረው በአዋጅ እንጂ በመግባቢያ ሰነድ ባለመሆኑ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ሀላፊዎች ለነባራዊ ሁኔታው የተሰጠው መልስ ለኦዲቱ አጥጋቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

71.ሚኒስቴር መ/ቤቱ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6/2 መሠረት ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የሚቀርብለት ጥያቄ መሠረት ከተጠቃለለው ፈንድ ላይ ክፍያ መፈጸም ሲገባው፤ አዋጁ በማይፈቅደውና ህጋዊነት በሌለው ባንኩ ውክልና ለሰጣቸው ለዘጠኙ ክልሎች እና ለሁለቱ ከተማ መስተዳድር የፋይናንስ ቢሮዎች ባቀረቡት ጥያቄ መሰረት ከተጠቃለለው የፈንዱ ገንዘብ ከ9 ቢሊዮን ብር በላይ ክፍያ መፈጸሙ የወጣው የመንግስት አዋጅ ተግባራዊ እንዳይሆን ከማድረጉም በተጨማሪ በአዋጁ ባንኩ ፈንዱን እንዲያስተዳድር የተመረጠበት ከአለው አደረጃጀት እና ሙያዊ አቅምን ከግምት ውሥጥ በማስገባት በፈንዱ የተሻለ ቁጥጥር ውጤታማ እንዲሆን ታሳቢ ያደረገ በመሆኑ፤ በህጋዊ መንገድ ገንዘቡን የማስተዳደር ስልጣን ላልተሰጣቸው አካላት ክፍያ እንዲፈጸም መደረጉ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ የተሰራጨው የመንግስት ገንዘብ ከታለመለት አላማ ውጪ ሊያደርጉ የሚችሉ የአደረጃጀት እና የአቅም ክፍተቶች እንዲፈጠሩ እና ፈንዱ ለአልተፈለገ ብክነት እና ምዝበራ እንዲጋለጥ ሊያደርግ ይችላል፡፡

ሚንስቴር መ/ቤቱ በክልሎች እና በከተማ መስተዳድር የፋይናንስ ቢሮዎች በፈንዱ አፈፃፀም ዙሪያ ክትትል እና ቁጥጥር ማድረጉን በተመከለተ

የፋይናንስ ቢሮዎች የፈንዱን ገንዘብ ለአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት ማስተላለፋቸውን በተመለከተ

72.ሚኒስቴር መ/ቤቱ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በአዋጁ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት ለክልል ፋይናንስ ቢሮዎች የሰጠውን ውክልና ተግባሪ እንዲያደርጉት በሰጠው መመሪያ መሰረት የዘጠኙ ክልሎች፣ የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተማ መስተዳድር የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮዎች ከአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት ጋር በገቡት የገንዘብ አስተዳደር ውል የፈንዱን ገንዘብ ለአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት ማስተላለፋቸውን ክትትል እና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡

73.ሆኖም እስከ ሰኔ 2010 ዓ/ም የትግራይ፣ አማራ፣ ኦሮሚያ ክልሎች እና የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮዎች ከአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት ጋር ገንዘቡን ለማስተዳደር ባደረጉት ስምምነት ሰነድ መሰረት የፈንዱን ገንዘብ ለአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት ማስተላለፋቸውን ነገር ግን ትግበራውን በተመለከተ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ለክልል ፋይናንስ ቢሮዎች የሰጣቸውን የስልጣን ውክልና እነዲተገበሩ በሰጠው አቅጣጫ መሰረት ክትትል እና ቁጥጥር እንዳላደረገላቸው የሚመለከታቸው የቢሮው የስራ ኃላፊዎች በተደረገላቸው ቃለ መጠይቅ እና ለኦዲቱ ከቀረቡ የሰነድ ማስረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

74.ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች በኦዲቱ መውጫ ስብሰባ በሰጡት መልስ፤ በ2009 እና በ2010 ዓ/ም ክልሎች በውክልናው በተሰጣቸው ተግባርና ኃላፊነት መሰረት የፈንዱን አፈጻጸም መተግበራቸው ወይም እንዲተገበሩ ክትትል አለማድረጋቸው፤ ሆኖም በ2011 ዓ/ም ክትትል ማድረግ መጀመራቸውን የደብዳቤ ቁጥር አሂከ6/65/40 በቀን 11/1/2011 በማስረጃ በማስደገፍ ገልጸዋል፡፡

75.ሚኒስቴር መ/ቤቱ የዘጠኙ ክልሎች፣ የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተማ መስተዳድር የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮዎች የፈንዱን ገንዘብ በወሰነው የማበደርያ ደንቦች እና ሁኔታዎች መሰረት ተግባራዊ ስለማድረጋቸው እንዲሁም ለተጠቃሚዎች ለማስተላለፍ ከአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት ጋር የገንዘብ አስተዳደር ውል መዋዋላቸውን ክትትል እና ቁጥጥር ባለማድረጉ፤ የክልሎች እና ከተማ መስተዳድር

ፋይናንስ ቢሮዎች የፈንዱን ገንዘብ ለተጠቃሚዎች ያስተላለፉበት ከአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት ጋር ያደረጉት የውል ስምምነት ሰነድ ወጥነት የሌለው እና በሚመለከተው አካል ተዘጋጅቶ ያልጸደቀ እንዲሆን አድርጎታል፤ ይህ ደግሞ ገንዘቡ ለተጠቃሚዎች ሲተላለፍ ችግሮች ሊፈጠሩ የሚችሉበት ዕድል ከፍ እንዲል ስለሚያደርግ ተመላሽ በሚደረገው ብድር ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ሊያሳድር ይችላል፡፡

የክልል ፋይናንስ ቢሮዎች የፈንዱን ሂሳብ አፈጻጸም የሚያሳይ ሪፖርት ለገንዘብ ሚኒስቴር ማቅረባቸውን ክትትልና ቁጥጥር መደረጉ በተመከለተ

76. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በአዋጁ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት ለክልል ፋይናንስ ቢሮዎች የሰጠውን ውክልና ተግባሪ እንዲያደርጉት በሰጠው መመሪያ መሰረት የዘጠኙ ክልሎች፣ የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተማ መስተዳድር የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮዎች ስለ ፈንዱ ገንዘብ አጠቃቀም ከአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት የሚቀርብላቸውን ሪፖርት በማጠቃለል በየስድስት ወሩ እንዲሁም የተመረመረ የፈንዱን ሂሳብ ከተሰጠው የኦዲት አስተያየት ጋር በየአመቱ ሂሳቡ በተመረመረ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ በፌደራል መንግስት የበጀት አመት ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ማቅረባቸውን ክትትል እና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡

77. ሆኖም የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በቀን 01/10/2009 ዓ/ም በደብዳቤ ቀጥር ማኢ-30/19/12 ባንኩ በአዋጁ ከተገለፀው ውጭ በውክልና ስልጣኑን ለሰጣቸው ለዘጠኙ ክልሎች እና ለሁለቱ ከተማ መስተዳድር የፋይናንስ ቢሮዎች በውክልና የተሰጣቸውን ኃላፊነት ተግባራዊ እንዲያደርጉት ባዘዘው መሰረት ክትትልና ቁጥጥር ያላደረገ ሲሆን፤ ነገር ግን ክልሎች የወሰዱትን ገንዘብ ስለማሰራጨታቸው እና በቀጣይ ደግሞ ገንዘብ እንዲላክላቸው ለመጠየቅ ከሚልኳቸው ደብዳቤዎች ውጪ የተመረመረ የፈንዱን ሂሣብ ከተሰጠው የኦዲት አስተያየት ጋር የሚያሳይ ሪፖርት ልከው እንደማያውቁ የሚመለከታቸው የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በቀን 26/11/2010 ዓ/ም በተደረገላቸው ቃለ መጠይቅ ገልጸዋል፡፡

78. በውክልና በተሰጣቸው ስልጣን መሰረት ስለፈንዱ ገንዘብ አጠቃቀም ከአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት በየስድስት ወሩ የተጠቃለለ፣ እንዲሁም በአንቀጽ 15/2 መሠረት የተመረመረ የፈንዱን ሂሣብ ከተሰጠው የኦዲት አስተያየት ጋር ያልቀረበላቸው መሆኑና በየዓመቱ ሂሳቡ በተመረመረ በአንድ ወር ውስጥ ባንኩን ወክለው ለገንዘብ ሚኒስቴር

ሪፖርት አለማቅረባቸው፤ እንዲሁም ሪፖርት እንዲያቀርቡ ህጋዊነትና ተከታታይነት ባለው መልኩ ክትትልና ቁጥጥር ያደረገላቸው አካል እንደሌለ የአማራ፣ትግራይ፣ የኦሮሚያ ክልል እና የአዲስ አበባ መስተዳድር የፋይናንስ ቢሮዎች እንዲሁም የብድርና ቁጠባ ተቋም አ/ማህበራት የሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡ እንዲሁም የገንዘብ ስርጭቱ እና ገንዘብ እንዲላክላቸው ስለመጠየቃቸው በሚያሳዩ ለገንዘብ ሚኒስቴር ከተላኩ የጽሁፍ ሰነዶች ለመረዳት ተችሏል፡፡

79. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች በኦዲቱ መውጫ ስብሰባ በሰጡት መልስ፤ በ2009 እና በ2010 ዓ/ም ክልሎች በውክልናው በተሰጣቸው ተግባርና ኃላፊነት መሰረት የፈንዱን አፈጻጸም መተግበራቸው ወይም እንዲተገብሩ ክትትል አለማድረጋቸው፤ ሆኖም በ2011 ዓ/ም ክትትል ማድረግ መጀመራቸውን የደብዳቤ ቁጥር አሂከ6/65/40 በቀን 11/1/2011 በማስረጃ በማስደገፍ ገልጸዋል፡፡

80. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የዘጠኙ ክልሎች፣ የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተማ መስተዳድር የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮዎች ስለ ፈንዱ ገንዘብ አጠቃቀም ከአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት የሚቀርብላቸውን ሪፖርት በማጠቃለል በየስድስት ወሩ እንዲሁም የተመረመረ የፈንዱን ሂሳብ ከተሰጠው የኦዲት አስተያየት ጋር በየአመቱ ሂሳቡ በተመረመረ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ በፌደራል መንግስት የበጀት አመት መሰረት ማቅረባቸውን ክትትል እና ቁጥጥር ባለማድረጉ ራሱ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የ2009 እና የ2010 በጀት ዓመት የተመረመረ የፈንዱን ሂሳብ ለሚኒስትሮች እና ለተወካዮች ምክር ቤት እንዳያቀርብ አድርጎታል፡፡

ክፍል ሦስት

የኦዲቱ መደምደሚያ (Audit Conclusion)

81. የገንዘብ ሚኒስቴር ህጋዊ የሆነ የአፈጻጸም መመሪያ በወቅቱ በማዘጋጀት ስራ ላይ እንዲውል ባለማድረጉ ለወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ ከተመደበው 10 **ቢሊዮን** ብር ውስጥ **ከ**9 **ቢሊዮን** ብር በላይ ያለ ህጋዊ መመሪያ ለተጠቃሚዎች እንዲሰራጭ ተደርጓል፡፡
82. የገንዘብ ሚኒስቴር የፈንዱን ገንዘብ በአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት በኩል ለተጠቃሚዎች የሚያስተላልፍበትን ደንቦችና ሁኔታዎች አዘጋጅቶ ስራ ላይ እንዲውል ባለማድረጉ ለወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ ከተመደበው 10 **ቢሊዮን** ብር ውስጥ **ከ**9 **ቢሊዮን** ብር በላይ ገንዘቡ ለተጠቃሚዎች የሚተላለፍበት ህጋዊ የሆነ ደንብ በሌለበት ወጪ ሆኖ ለተጠቃሚዎች እንዲሰራጭ ተደርጓል፡፡
83. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ በተመለከተ በአዋጅ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት ለመወጣት የሚያስችል አደረጃጀት እና የመረጃ ልውውጥ ስርአት ያለው ቢሆንም የፈንዱን አፈጻጸም ህጋዊና ውጤታማ ለማድረግ በአዋጅ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት አዋጁን መሰረት ባደረገ ሁኔታ ስራ ላይ እንዲውል አላደረገም፡፡
84. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ አዋጅ መሰረት ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በሚደርሰው የፈንዱን አጠቃቀም መግለጫና ሪፖርት በተጠቃለለው ዓመታዊ የመንግስት ሂሣብ ሪፖርት ውስጥ በማካተት በ2009 እና በ2010 በጀት ዓመት በየደረጃው ለሚኒስትሮች ምክር ቤት እና ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አላቀረበም፡፡
85. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የየክልሉን ወጣቶች ቁጥር መሠረት በማድረግ ከፈንዱ ገንዘብ ላይ ለየክልሉ ሊከፋፈል የሚገባውን ድርሻ በማስላት በአዋጅ ስልጣን ለተሰጠው ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በተሟላ መልኩ ማሳወቅ ሲገባው፤ ከ10 ቢሊዮን ብር ውስጥ 5 ቢሊዮን ብር ባቻ ነው ባንኩ እንዲያውቀው የተደረገው፤ ነገር ግን ሙሉ በሙሉ የክልሎች ድርሻ የማሳወቅ ስራ ሳይሰራ ከ9.1 ቢሊዮን ብር በላይ የፈንዱ ገንዘብ ከመንግስት ካዝና ወጪ ተደርጎ ለተጠቃሚዎች እንዲሰጥ እንዲተላለፍ ተደርጓል፡፡

86. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በተዘዋዋሪ ፈንድ አዋጅ አንቀጽ 6/2 መሠረት ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በሚቀርብለት ጥያቄ መሠረት ከተጠቃለለው ፈንድ ላይ ክፍያ መፈጸም ሲገባው፤ ህጋዊነት ለሌላቸውና በአዋጁ ስልጣን ላልተሰጣቸው ለዘጠኙ ክልሎችና ለሁለቱ ከተማ መስተዳድር የፋይናንስ ቢሮዎች **ከ9 ቢሊዮን** ብር በላይ ክፍያ ፈጽሟል፡፡

87. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የዘጠኙ ክልሎች፣ የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተማ መስተዳድር የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮዎች ተፈጻሚ እንዲያደርጉት በሰጠው አቅጣጫ መሰረት፤ ከአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት ጋር በገቡት የገንዘብ አስተዳደር ውል መሰረት የፈንዱን ገንዘብ ለአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት ማስተላለፋቸውን ክትትል እና ቁጥጥር አላደረገም፡፡

88. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የዘጠኙ ክልሎች፣ የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተማ መስተዳድር የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮዎች ህጋዊ ያልሆነ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ውክልና ተፈጻሚ እንዲያደርጉት በሰጠው አቅጣጫ መሰረት፤ ስለ ፈንዱ ገንዘብ አጠቃቀም ከአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት የሚቀርብላቸውን ሪፖርት በማጠቃለል በየስድስት ወሩ እንዲሁም የተመረመረ የፈንዱን ሂሳብ ከተሰጠው የኦዲት አስተያየት ጋር በየአመቱ ሂሳቡ በተመረመረ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ በፌደራል መንግስት የበጀት አመት መሰረት ለገንዘብ ሚኒስቴር ማቅረባቸውን ክትትል እና ቁጥጥር አላደረገም፡፡

ክፍል አራት

የኦዲቱ ማሻሻያ ሀሳብ (Recommendation)

89. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ህጋዊ የሆነ የአፈጻጸም መመሪያ በወቅቱ በማውጣት ተግባራዊ እንዲሆን ባለማድረጉ ለወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ ከተመደበው 10 ቢሊዮን ብር ከ9.1 ቢሊዮን ብር በላይ ለተጠቃሚዎች እንዲሰራጭ የተደረገበትን ሁኔታ ተገቢውን ማጣራት በማድረግና የነበሩ ችግሮችን በመለየት፤ የኢትዮጵያ ተዘዋዋሪ ፈንድ ቀጣይነት ባህሪ ስላለው ተገቢውን ጥናት በማድረግ የአፈጻጸም መመሪያ በማውጣት ተግባራዊ እንዲሆን ሊያደርግ ይገባል፡፡

90. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ ከተመደበው 10 ቢሊዮን ብር ወስጥ ከ9.1 ቢሊዮን ብር በላይ ወጪ ሆኖ ለተጠቃሚዎች እስከ ተሰራጨበት ጊዜ ድረስ የፈንዱን ገንዘብ ባንኩ በአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት በኩል ለተጠቃሚዎች የሚያስተላልፍበትን ደንቦችና ሁኔታዎች በመወሰን ስራ ላይ እንዲውል ያልተደረገበት ምክንያት በመለየት እንዲሁም እስካሁን ለተጠቃሚዎች የተሰራጨ የፈንዱ ገንዘብ ህጋዊ መንገድ የሚዝበት ሁኔታ በመፍጠር ወጥ የሆነ ደንብና ሁኔታ በማውጣት ተግባራዊ እንዲሆን ቢያደርግ ለቀጣይም ሆነ አሁን በብድር የተሰጠ የፈንዱ ገንዘብ ተመላሽ የሚሆንበት እድል የሰፋ እንዲሆን ከማድረጉም ባሻገር የወሰዱትን ብድር በውሉ ስምምነት መሰረት የማይመልሱ ተጠቃሚዎች በህግ ተጠያቂ በማድረግ ገንዘቡን እንዲመልሱ የሚደረገው ጥረት ውጤታማ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

91. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ በተመለከተ በአዋጅ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት ለመወጣት የሚያስችል አደረጃጀት እና የመረጃ ልውውጥ ስርአት ስራ ላይ እንዲውል በማድረግ የፈንዱን አፈጻጸም የተሻለ በማድረግ የተመደበው 10 ቢሊዮን ብር ለተባለለት አላማ እንዲውል ሊያደርግ ይገባል፡፡

92. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ አዋጅ መሰረት ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በሚደርሰው የፈንዱን አጠቃቀም መግለጫና ሪፖርት በተጠቃለለው ዓመታዊ የመንግስት ሂሣብ ሪፖርት ውስጥ በማካተት በ2009 እና በ2010 በጀት ዓመት በየደረጃው ለሚኒስትሮች ምክር ቤት እና ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መላክ ሲገባው ያላከበትን ችግር በመለየት እስካሁን ያለውን የፈንዱን አጠቃቀም ሪፖርት

እንዲላክ በማድረግ በሚቀጥለው በጀት አመት ውስጥ በማካተት ሪፖርት ሊያደርግ ይገባል፡፡ ይህ ደግሞ በፈንዱ ዙሪያ ያሉ በርካታ ችግሮች በወቅቱ የሚመለከታቸው የሀገሪቷ የበላይ ኃላፊዎች የመፍትሄ አቅጣጫ በማፈላለግ ለተጠቃሚዎች የተሰጠውን ከ9.1 ቢሊዮን ብር በላይ የፈንዱ ገንዘብ የተጋረጠበትን ያለመመለስ ስጋት እንዲቀንስ ያደርጋል፡፡

93. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የየክልሉን ወጣቶች ቁጥር መሠረት በማድረግ ከ10 ቢሊዮን የፈንዱ ገንዘብ ላይ ለየክልሉ ሊከፋፈል የሚገባውን ድርሻ በማስላት በአዋጅ ስልጣን ለተሰጠው ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በተሟላ መልኩ ሳያሳውቅ ከ9.1 ቢሊዮን ብር በላይ ወጪ ሆኖ ለተጠቃሚዎች እንደሰጥ የተደረገበት ምክንያት በግልጽ በመለየት አሰራሩ በአዋጁ መሰረት ህጋዊነት ያለው መንገድ እንዲከተል እና ክልልሎች ያላቸውን ድርሻ በተሟላ መልኩ እንዲያውቁት ሊያደርግ ይገባል፡፡

94. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በተዘዋዋሪ ፈንድ አዋጅ አንቀጽ 6/2 መሠረት ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በሚቀርብለት ጥያቄ መሠረት ከተጠቃለለው ፈንድ ላይ ክፍያ መፈጸም ሲገባው ህጋዊነት ለሌላቸውና በአዋጁ ስልጣን ላልተሰጣቸው ለዘጠኙ ክልሎችና ለሁለቱ ከተማ መስተዳደር የፋይናንስ ቢሮች ከ9.1 ቢሊዮን ብር በላይ ክፍያ ሊፈጽም የቻለበት ምክንያት እና ለዚህ ኃላፊነት ሊወስድ የሚችል አካል በግልጽ በመለየት አሰራሩ በአዋጁ መሰረት ህጋዊ አሰራር የተከተለ እንዲሆን ሊያደርግ ይገባል፡፡

95. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የዘጠኙ ክልሎች፣ የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተማ መስተዳድር የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮዎች ከባንኩ የተሰጣቸውን ውክልና ተፈጻሚ እንዲያደርጉት በሰጠው አቅጣጫ መሰረት፣ ስለ ፈንዱ ገንዘብ አጠቃቀም ከአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት የሚቀርብላቸውን ሪፖርት በማጠቃለል በየስድስት ወሩ እንዲሁም የተመረመረ የፈንዱን ሂሳብ ከተሰጠው የኦዲት አስተያየት ጋር በየአመቱ ሂሳቡ በተመረመረ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ በፌደራል መንግስት የበጀት አመት መሰረት ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ማቅረባቸውን ክትትል እና ቁጥጥር ያላደረገበት ምክንያት በግልጽ በመለየት አስፈላጊውን ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ በአዋጁ በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ለሚመለከታቸው አካላት ሪፖርቶች እንዲላኩ ሊያደርግ ይገባል፡፡

በኦዲቱ ወቅት ለተደረገልን ትብብር እናመሰግናለን!

አባሪዎች

አባሪ 1- የገንዘብ ሚኒስቴር የመመዘኛ መስፈርት

የኦዲት የመመዘኛ መስፈርቶቹን ለማዘጋጀት መሰረት ከሆኑት ዋና ዋናዎቹ የኢትዮጵያ ወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ አዋጅ 995/2009 እና የገንዘብ ሚኒስቴር በቀን 01/10/2009 ዓ/ም በደብዳቤ ቀጥር ማኢ-30/19/12 የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በአዋጅ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት በውክልና ለዘጠኙ ክልሎች እና ለሁለቱ ከተማ መስተዳድሮች የፋይናንስ ቢሮዎች የሰጠው ኃላፊነት እንዲተገበር በሚኒስቴር መ/ቤቱ አቅጣጫ የተሰጠበት ሰነድ ናቸው፡፡

ተ/ቁ	የመመዘኛ መስፈርት Evaluative Criteria
1.	ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ አዋጅ ቁጥር 995/2009 የአፈጻጸም መመሪያ በማውጣት የሚመለከታቸው አካላት እንዲተገብሩት ህጋዊ በሆነ መልኩ ሊያሰራጭ እና ራሱም ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ **ምንጭ፡-/የኢትዮጵያ ወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር 995/2009 ዓ/ም አንቀጽ 16 መመሪያ የማውጣት ስልጣን/**
2.	የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ባንኩ የፈንዱን ገንዘብ በአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት በኩል ለተጠቃሚዎች የሚያስተላልፍበትን ደንቦችና ሁኔታዎች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመመካከር ሊወስን ይገባል፡፡ **/ምንጭ፡- የኢትዮጵያ ወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር 995/2009 ዓ/ም የሚኒስትሩ ተግባርና ኃላፊነት አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 2/**
3.	ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአዋጅ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት ለመወጣት የሚያስችል መዋቅር እና የሰው ኃይለል ሊኖረው ይገባል፡፡ **/መልካም ተሞኩሮ/**
4.	ሚኒስቴር መ/ቤቱ የወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድን በተመለከተ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር መረጃ ለመለዋወጥ የሚያስችለው የመረጃ ልውውጥ ስርአት በመዘርጋት ተግባራዊ ሊያደርግ ይጋባል፡፡ **/መልካም ተሞኩሮ/**
5.	የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ከባንኩ የሚደርሰውን የፈንዱ አጠቃቀም መግለጫና ሪፖርት በተጠቃለለው ዓመታዊ የመንግስት ሂሣብ ሪፖርት ውስጥ

	በማካተት በየደረጃው ለሚኒስትሮች ምክር ቤት እና ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሊያቀርብ ይገባል፡፡ **/ምንጭ፡- የኢትዮጵያ ወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ ለማቋቋም የወጣው አዋጅቁጥር 995/2009 ዓ/ም የሚኒስትሩ ተግባርና ኃላፊነት አንቀጽ 9 ንዕስ አንቀጽ 4/**
6.	የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር የየክልሉን ወጣቶች ቁጥር መሠረት በማድረግ ከፈንዱ ገንዘብ ላይ ለየክልሉ ሊከፋፈል የሚገባውን ድርሻ በማስላት ለባንኩ ሊያሳውቅ ይገባል፡፡ **/ምንጭ፡- የኢትዮጵያ ወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ ለማቋቋም የወጣው አዋጅቁጥር 995/2009 ዓ/ም የሚኒስትሩ ተግባርና ኃላፊነት አንቀጽ 9 ንዕስ አንቀጽ 1 /**
7.	የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6/2 መሠረት ከባንኩ የሚቀርብለት ጥያቄ መሠረት ከተጠቃለለው ፈንድ ላይ ክፍያ ሊፈጽም ይገባል፡፡ **/ምንጭ፡- በየኢትዮጵያ ወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ ለማቋቋም የወጣው አዋጅቁጥር 995/2009 ዓ/ም የሚኒስትሩ ተግባርና ኃላፊነት አንቀጽ 9 ንዕስ አንቀጽ 3 /**
8.	ሚኒስቴር መ/ቤቱ የዘጠኙ ክልሎች፣ የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተማ መስተዳድር የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮዎች ከአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት ጋር በገቡት የገንዘብ አስተዳደር ውል መሰረት የፈንዱን ገንዘብ ለአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት ማስተላለፋቸውን ክትትል እና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡ **ምንጭ፡- ዘጠኙ ክልሎች እና ሁለቱ ከተማ መስተዳድር የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮዎች የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ፈንዱን የማስተዳደር ኃላፊነት በውክልና ተረክበው እንዲተገብሩ በገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ጸድቆ ተግባራዊ እንደሆን በክልሎችና መስተዳድሮች፣ በገ/ኢ/ት/ሚኒስቴር እና በኢ/ንግድ ባንክ መካከል ከተደረገ የወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ የመግባብያ ሰነድ/ ቁጥር ማኢ-30/19/12 ቀን 01/10/09**
9.	ሚኒስቴር መ/ቤቱ የዘጠኙ ክልሎች እና የሁለቱ ከተማ መስተዳድር የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮዎች ስለ ፈንዱ ገንዘብ አጠቃቀም ከአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት የሚቀርብላቸውን ሪፖርት በማጠቃለል በየስድስት ወሩ እንዲሁም የተመረመረ

	ፈንዱን ሂሳብ ከተሰጠው የኦዲት አስተያየት ጋር በየአመቱ ሂሳቡ በተመረመረ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ በፌደራል መንግስቱ የበጀት አመት መሰረት ለሚኒስትሩ ማቅረባቸውን ክትትል እና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡ **ምንጭ፡- በቁጥር ማኢ-30/19/12 በቀን 01/10/2009 ዓ/ም ዘጠኙ ክልሎች እና ሁለቱ ከተማ መስተዳድር የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮዎች የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ፈንዱን የማስተዳደር ኃላፊነት በውክልና ተረክበው እንዲተገብሩ በገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ጸድቆ ተግባራዊ እንደሆን የተጻፈ ደብዳቤ እና በክልሎችና መስተዳድሮች፣ በገ/ኢ/ት/ሚኒስቴር እና በኢ/ንግድ ባንክ መካከል የተደረገ የወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ የመግባቢያ ሰነድ/**